የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፰
አዲስ አበባ ሕዳር ፳ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No.8
ADDIS ABABA 29th November, 2018

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፯/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ……………………………ገጽ ፲ሺ፮፻፴፬

## Content

Proclamation No.1097/2018

Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation.--………………Page 10634

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፯/፪ሺ፲፩

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት ሕገ-መንግሥታዊ ሥልጣንና ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችለው አወቃቀር አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለዉን ለዉጥ ውጤታማ፣ ዘላቂ እና ተቋማዊ ለማድረግ፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር እንደገና መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### PROCLAMATION NO.1097/2018

**A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE DEFINITION OF THE POWERS AND DUTIES OF THE EXECUTIVE ORANGS OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF EHTIOPIA**

**WHEREAS**, a government organization that allows the proper exercise of the constitutional powers and duties of the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is necessary;

**WHEREAS**, such government organization is essential for the success, sustainability and institutionalization of the reform underway in Ethiopia;

**WHEREAS**, it has been found necessary to redefine the organization, powers and duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby Proclaimed as follows.

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፯/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

፩. "ሕገ-መንግሥት" ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ነው።

፪. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ ፵፯ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል።

፫. "ምክር ቤት" ማለት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው።

፬. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር የሴት ፆታንም ይጨምራል።

## ክፍል ሁለት

## ስለጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ስለምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩና ስለሚኒስትሮች ምክር ቤት

### ፫. የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣንና ተግባር በሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ ፸፬ የተመለከተው ነው።

### ፬. የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣንና ተግባር በሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ ፸፭ የተመለከተው ነው።

### ፭. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር በሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ ፸፯ የተመለከተው ነው።

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1097/2018 "

### 2. Definition

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1. "Constitution" means the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.
2. "Regional State" means any state referred to under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations.
3. "Council" means the Council of Ministers;
4. Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## PART TWO

## THE PRIME MINISTER, THE DEPUTY PRIME MINISTER, AND THE COUNCIL OF MINISTERS

### 3. Powers and Duties of the Prime Minister

The powers and duties of the Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia are those defined under Article 74 of the Constitution.

### 4. Powers and Duties of the Deputy Prime Minister

The powers and duties of the Deputy Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia are those defined under Article 75 of the Constitution.

### 5. Powers and Duties of the Council of Ministers

The powers and duties of the Council of Ministers of the Federal Democratic Republic of Ethiopia are those defined under Article 77 of the Constitution.

**፮. <u>የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት</u>**

፩. የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል:-

ሀ) ጠቅላይ ሚኒስትር፣

ለ) ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር፣

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀፅ፱ የተመለከቱትን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች የሚመሩ ሚኒስትሮች፣ እና

መ) በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ ሌሎች ባለስልጣኖች።

፪. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ (ሐ) የተመለከተው ማንኛውም ሚኒስትር በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ የሚኒስቴሩ ሚኒስትር ዴኤታዎች በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ይሳተፋሉ። ከአንድ በላይ ሚኒስትር ዴኤታዎች ካሉና ሚኒስትሩ በተለይ ካልወከለ በሹመት ቅድሚያ ያለው ሚኒስትር ዴኤታ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ይሳተፋል።

**፯. <u>የሚኒስትሮች ምክር ቤት የስብሰባ ስነ-ሥርዓት</u>**

፩. የሚኒስትሮች ምክር ቤት፡-

ሀ) ሥራውን በአግባቡ ለማካሄድ አስፈላጊው የውስጥ ደንብ ይኖረዋል፤

ለ) በውስጥ ደንቡ በሚወሰነው መሠረት መደበኛ እና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያካሂዳል፤

ሐ) ስብሰባ ላይ ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይኖራል፤

መ) የሚያስተላልፈው ውሳኔ በተባበረ ድምፅ ይሆናል፣ በተባበረ ድምፅ መወሰን ካልተቻለ በአብላጫ ድምፅ ይወሰናል፤ የተሰጠው ድምፅ እኩል ከሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

፪. ጠቅላይ ሚኒስትሩ፡-

ሀ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት አጀንዳ የማስያዝ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለምክር ቤቱ በአጀንዳ የሚቀርቡ ጉዳዮችን ይወስናል፤

ለ) የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል፤

ሐ) ለምክር ቤቱ በአጀንዳ የቀረበ ጉዳይ በሚመለከተው የምክር ቤቱ ኮሚቴ መታየት የሚያስፈልገው ሆኖ ካገኘው ስብሰባውን ለሌላ ጊዜ ያስተላልፋል።

**6. <u>Members of the Council of Ministers</u>**

1. The Council of Ministers shall have the following members:
   a. the Prime Minister;
   b. the Deputy Prime Minister;
   c. Ministers heading the Ministries specified under Article 9 of this Proclamation; and
   d. other Officials to be designated by the Prime Minister.
2. Where any Minister of a Ministry referred to in sub- article 1(c) of this Article can not attend the meeting of the Council, the Minister of State of the Ministry shall take part in the meeting of the Council. Where there are more than one ministers of state and no specific delegation has been given by the Minister, the Minister of State who is senior by appointment shall take part in the meeting of the Council.

**7. <u>Meeting Procedure of the Council of Ministers</u>**

1. The Council of Ministers shall:
   a. have its own internal procedural rules for a proper conduct of its activities;
   b. conduct ordinary and extraordinary meetings in accordance with its procedural rules;
   c. have a quorum where more than half of its members are present;
   d. pass decisions by consensus, or failing that, by majority vote; where the Council has given an equal number of votes for and against a decision, the Prime Minister shall have the casting vote.
2. The Prime Minister shall:
   a. without prejudice to the rights of the members of the Council of Ministers to propose agenda items, determine the agenda of the Council;
   b. preside over the meetings of the Council;
   c. adjourn the meetings of the Council under circumstances where he finds it necessary to refer a matter included in the Council's agenda to the relevant Committee of the Council.

፫. ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል።

**፰. <u>የሚኒስትሮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች</u>**

፩. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባሩን ለመወጣት ይረዳው ዘንድ የምክር ቤቱ አባላት የሚገኙባቸው ልዩ ልዩ ቋሚ ኮሚቴዎች ሊያቋቁም ይችላል።

፪. የቋሚ ኮሚቴዎች ሥልጣንና ተግባር በምክር ቤቱ የውስጥ ደንብ ይወሰናል።

## ክፍል ሶስት
## ስለሚኒስቴሮች

**፱. <u>የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች መቋቋም</u>**

በዚህ አዋጅ የሚከተሉት ሚኒስቴሮች ተቋቁመዋል፡-

፩/ የሰላም ሚኒስቴር
፪/ የአገር መከላከያ ሚኒስቴር
፫/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
፬/ የገንዘብ ሚኒስቴር
፭/ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ
፮/ የግብርና ሚኒስቴር
፯/ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
፰/ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር
፱/ የትራንስፖርት ሚኒስቴር
፲/ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
፲፩/ የውሃ፣ መስኖና ኤነርጂ ሚኒስቴር
፲፪/ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
፲፫/ የትምህርት ሚኒስቴር
፲፬/ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
፲፭/ የጤና ሚኒስቴር
፲፮/ የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር
፲፯/ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
፲፰/ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
፲፱/ የገቢዎች ሚኒስቴር

**፲. <u>የሚኒስቴሮች የወል ሥልጣንና ተግባር</u>**

እያንዳንዱ ሚኒስቴር፡-

3. In the absence of the Prime Minister, the Deputy Prime Minister shall preside over the meetings of the Council.

**8. <u>Standing Committees of the Council of Ministers</u>**

1. The Council of Ministers may, with a view to facilitating its functions, establish various standing committees comprising of its members;
2. The powers and duties of the Standing Committees shall be defined in the internal rules of the Council.

## PART THREE
## MINISTRIES

**9. <u>Establishment of Ministries</u>**

The following ministries are established by this Proclamation:

1. the Ministry of Peace;
2. the Ministry of National Defense;
3. the Ministry of Foreign Affairs;
4. the Ministry of Finance;
5. the Attorney General;
6. the Ministry of Agriculture;
7. the Ministry of Trade and Industry;
8. the Ministry of Innovation and Technology;
9. the Ministry of Transport;
10. the Ministry of Urban Development and Construction;
11. the Ministry of Water, Irrigation and Energy;
12. the Ministry of Mines and Petroleum;
13. the Ministry of Education;
14. the Ministry of Science and Higher Education;
15. the Ministry of Health;
16. the Ministry of Women, Children and Youth;
17. the Ministry of Labor and Social Affairs;
18. the Ministry of Culture and Tourism;
19. the Ministry of Revenues.

**10. <u>Common Powers and Duties of Ministries</u>**

Each ministry shall have the power and duties to:

፩/ በሥራው መስክ፡-

ሀ) የጥናትና ምርምር ተግባራትን ያከናውናል፣ በዘርፉ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀነባብራል፣ ያሰራጫል፤

ለ) በጥናት ላይ የተመሠረቱ ፖሊሲዎችን ያመነጫል፤

ሐ) የፌደራል መንግሥት ሕጎችን ያመነጫል፣ ያስፈጽማል፤

መ) የፌደራል መንግሥቱን ፖሊሲ በሥራ ላይ ለማዋል ከሌሎች ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ጋር አስፈላጊውን ቅንጅት በመመሥረት ይሠራል፤

ሠ) ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

ረ) የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፣ የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣ ዉጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤

ሰ) ለክልሎች እንዳስፈላጊነቱ ድጋፍና ምክር ይሰጣል፤ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች በሰላም ሚኒስቴር አስተባባሪነት የተቀናጀ ድጋፍ ያደርጋል፤

ሸ) ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤

ቀ) በሕግ መሠረት ውሎችንና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ይፈራረማል፤

፪. በማቋቋሚያ ሕጎቻቸው ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫ ተጠሪ የተደረጉለትን አስፈጻሚ አካላት አፈጻጸም በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል ፤ አደረጃጀቶቻቸውን እንዲሁም የሥራ ፕሮግራሞቻቸውንና በጀቶቻቸውን መርምሮ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል እንዲቀርቡ ይወስናል፤

፫. በሚያዘጋጃቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችን፣የሕፃናትንና የወጣቶችን ተጠቃሚነት ያረጋግጣል፤

፬. የአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎች በኃላፊነቱ ክልል የእኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፭. በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጎች የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

፮. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሌላ የፌደራል ወይም የክልል አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

1. In its area of jurisdiction:
   a. undertake research and studies; gather, synthesize, and disseminate information;
   b. formulate evidence-based policies;
   c. initiate federal laws, and implement the same;
   d. work in coordination with other ministries to implement policies of the Federal Government;
   e. prepare plans and budgets, and implement same upon approval;
   f. undertake capacity building activities; implement, cause the implementation, and ensure the effectiveness of reform and good governance activities;
   g. provide, as necessary, assistance and advice to Regional States; and provide coordinated support to Regional States eligible for affirmative support as coordinated by the Ministry of Peace;
   h. provide proper support to the develop ment of pastoral and semi-pastoral areas;
   i. enter into contracts and international agreements in accordance with law;
2. Direct and coordinate the performances of the executive organs made accountable to it under the laws establishing them or under Article 33 of this Proclamation; review their organizational structures as well as their work programs and budgets, and submit same to the appropriate government organs for approval;
3. Ensure that the policies, laws, development programs and projects it formulates benefit women, children and youth;
4. Create,within the purview of its authority, conditions whereby persons with disabilities, the elderly, and segments of society vulnerable to social and economic problems benefit from equal opportunities and full participation;
5. Exercise the powers and duties given to it under this Proclamation and other laws;
6. Where necessary,delegate part of its powers and duties to other Federal or Regional State Organ;

፯. ስለሥራው ክንዋኔ በየወቅቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ እና ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ሪፖርት ያቀርባል፤

**፲፩. የሚኒስትሮች ተጠሪነትና ኃላፊነት**

እያንዳንዱ ሚኒስትር፡-

፩. ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ይሆናል፤

፪. የሚመራውን ሚኒስቴር ይወክላል፣ ሥልጣንና ተግባሩን ሥራ ላይ ያውላል፤

፫. ለሚኒስቴሩ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

፬. በሚኒስቴሩ ውስጥ የአፈጻጸም አመራር ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል።

**፲፪. የሚኒስትር ዴኤታዎች ተጠሪነትና ኃላፊነት**

፩. የእያንዳንዱ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ሆኖ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

፪. ሚኒስትሩ በማይኖርበት ጊዜ ሚኒስትር ዴኤታው ተክቶት ይሠራል፤ ከአንድ በላይ ሚኒስትር ዴኤታዎች ካሉና ሚኒስትሩ በተለይ ካልወከለ በሹመት ቅድሚያ ያለው ሚኒስትር ዴኤታ ተክቶት ይሠራል።

**፲፫. የሰላም ሚኒስቴር**

፩/ የሰላም ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) ሰላምን ለማስጠበቅ አግባብ ካላቸው የፌደራልና የክልል መንግሥታት አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤ የአገርና ሕዝብ ሰላም፣ ደህንነትና ነፃነት እንዲከበሩ የሚያስችል ስልት ይነድፋል፤ የግንዛቤና የንቅናቄ ሥራዎችን ያከናውናል፤

ለ) ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር በመተባበር በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል የሚኖሩ ዜጎች ተገቢውን ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

ሐ) በተለያዩ ኃይማኖቶችና እምነቶች ተከታዮች፣ እንዲሁም በተለያዩ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መካከል ሰላምና መከባበር እንዲሰፍን ለማድረግ አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት፣ የባህልና የኃይማኖት ተቋማት፣ እንዲሁም ከሌሎች አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፤

7. Submit periodic performance reports to the Prime Minister, Council of Ministers, and other relevant bodies.

**11. Accountability and Responsibility of Ministers**

Each minister shall:

1. be accountable to the Prime Minister and the Council of Ministers;
2. represent the Ministry he runs and exercise its powers and duties;
3. effect payments in accordance with the budget and work programs approved for the Ministry;
4. ensure the implementation of performance management system with in the Ministry.

**12. Accountability and Responsibility of Ministers of State**

1. Each Minister of State of a Ministry shall be accountable to the Minister and shall carry out the responsibilities specifically entrusted to him.
2. The Minister of State shall, in the absence of the Minister, acton his behalf. Where there are more than one ministers of state and no specific delegation has been given by the Minister, the Minister of State who is senior by appointment shall act on behalf.

**13. Ministry of Peace**

1. The Ministry of Peace shall have powers and duties to:
   a. work in cooperation with concerned Federal and Regional State government organs to ensure the maintenance of public order; develop strategies, and undertake awareness creation and sensitization activities to ensure the peace, security and freedom of the country and its people;
   b. in collaboration with relevant Regional Organs, facilitate the provision of proper protection to citizens living in any part of the country;
   c. work in cooperation with relevant government organs, cultural and religious organizations, and other pertinent bodies to ensure peace and mutual respect among followers of different religions and beliefs, as well as nations, nationalities and peoples;

መ) በወሳኝ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጠር አግባብ ያላቸውን አካላት ያስተባብራል፤ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለመንግሥት ያቀርባል፤ ሲወሰንም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ሠ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አገራዊ አንድነትና መግባባትን የሚያጎለብት የባህል ልውውጥ፣ የስነ-ዜጋ ትምህርት እና ኪነ-ጥበብ የሚስፋፋበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ረ) በግለሰቦችና በቡድኖች መካከል የሰላም፣ የመከባበርና የመቻቻል ባህል እንዲዳብር የግንዛቤና ንቅናቄ ስልቶችን ይቀይሳል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፤

ሰ) ለአካባቢያዊ ግጭቶች መንስኤ የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት ይለያል፤ ኅብረተሰቡ ወደ ግጭትና አለመረጋጋት እንዳያመራ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን የሚያመለክት ጥናት ያቀርባል፣ ሲወሰንም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሸ) የሃይማኖት ድርጅቶችንና ማኅበራትን ይመዘግባል፤

ቀ) የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነትና የፋይናንስ ደኅንነት ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፤

በ) የፌደራል ፖሊስ ሥራዎች በአግባቡ መከናወናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ተ) የዜግነት፣ የብሔራዊ መታወቂያ፣ ኢሚግሬሽንና ፓስፖርት፣ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥራዎችን ይመራል፤

ቸ) የስደተኞች፣ የፖለቲካ ጥገኞችና ወደ አገር ተመላሾችን ጉዳዮች ይመራል፤

ኀ) ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት ያደርጋል፤ የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራርን በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፤

ነ) የጦር መሣሪያ፣ የተኩስ መሣሪያ ወይም ፈንጂ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ይወስናል፤ እነዚህን መሣሪያዎች ለመያዝ፣ ለመጠቀም እንዲሁም ለመሸጥ የሚያስፈልገውን ቅድመ-ሁኔታ ይወስናል፤

d. in cooperation with the relevant actors, work towards the creation of national consensus on critical national issues; propose recommendations to the government, and upon approval, follow up their implementation;

e. in cooperation with concerned bodies, promote the enhancement of cultural exchange, civic education, and artistic works that build national unity and consensus;

f. develop awareness creation and sensitization strategies to foster a culture of respect and tolerance among individuals and groups, and follow up their implementation;

g. identify factors serving as causes of conflicts among communities; submit a study proposing recommendations to keep communities away from conflicts and instability, and implement same upon approval;

h. register religious organizations and associations;

i. oversee and follow up national intelligence and security, as well as information network and financial security functions;

j. supervise andfollow up the proper execution of functions relating to Federal Police

k. lead and follow up citizenship, national identification card, immigration, passport and vital events registration or issuance functions;

l. lead and follow up the affairs of immigrants, political asylum seekers and returnees;

m. make appropriate preparations for natural and man-made disasters; lead and follow up national disaster risk management;

n. determine conditions for the utilization of arms, firearms, or explosives; determine requirements to carry, use and sell these weapons;

ኘ) በፌደራል መንግሥትና በክልሎች መካከል በመግባባትና በአጋርነት ላይ የተመሠረተ መልካም ግንኙነትና ትብብር እንዲኖር በማድረግ የፌደራል ሥርዓቱ እንዲጠናከር የግንኙነቱ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤

አ) የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፵፰ እና ፷፪ (፮) እንዲሁም ሌሎች አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በክልሎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤

ከ) አግባብ ያላቸው ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ከክልሎች ጥያቄ ሲቀርብ በክልሎች ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች በዘላቂነት የሚፈቱበትን መፍትሔ ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ኸ) ፌደራል መንግሥቱ በክልሎች ጉዳይ ጣልቃ እንዲገባ ሲወሰን አፈጻጸሙን ያስተባብራል፤

ወ) ለክልሎች በተለይም ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ትኩረት በመስጠት ድጋፍ ያደርጋል፤ ሌሎች የፌደራል መንግሥት አካላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢ እንዲሁም ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች የሚያደርጓቸውን ድጋፎች ያስተባብራል፣ ያቀናጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ዐ) አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራትን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያስተባብራል።

፪. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎችና ድንጋጌዎች ለፌደራልና አርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለሰላም ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## ፲፬. <u>የአገር መከላከያ ሚኒስቴር</u>

የአገር መከላከያ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩. የአገሪቱን የግዛት ሉዓላዊነት ያስከብራል፤ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ከአደጋና ጥቃት ይከላከላል፤

፪. አገር መከላከልን በሚመለከት አግባብ ያላቸውን የፌደራልና የክልል አካላት በማስተባበር ይሠራል፤

o. serve as a focal point of the federal-regional relationship to strengthen the federal system by cultivating good relationship and cooperation between the Federal Government and Regional States based on mutual understanding and partnership;

p. with out prejudice to the provisions of Article 48 and Article 62(6) of the Constitution and other relevant provisions, facilitate the resolution of disputes arising between Regional States;

q. with out prejudice to the provisions of the relevant laws and upon the request of Regional States, devise and implement sustainable solutions to disputes and conflicts that may arise within Regional States;

r. coordinate the implementation of decisions authorizing the intervention of the Federal Government in the affairs of Regional States;

s. provide assistance to Regional States particularly to those that need special support; coordinate, integrate and follow up supports given by other federal organs to pastoralists, semi-pastoralists and Regional States that need special support;

t. in collaboration with concerned organs coordinate activities that enable pastoralists and semi-pastoralists to become beneficiaries of social and economic developments.

2. The powers and duties given to the Ministry of Federal and Pastoralist Development Affairs by the provisions of other laws currently in force are hereby vested in the Ministry of Peace.

## 14. <u>Ministry of National Defense</u>

The Ministry of National Defense shall have the powers and duties to:

1. defend the territorial integrity of the country; protect and defend the Constitutional order form threats and attacks;
2. work by coordinating federal and regional organs relevant in defending the country;

፫. በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፤

፬. መከላከያ ሠራዊት ያቋቁማል፣ ያስታጥቃል፣ ይቆጣጠራል፣ የውጊያ ብቃቱን ያረጋግጣል፤

፭. የመከላከያ ሠራዊት ማሠልጠኛ ተቋማት እንዲደራጁ ያደርጋል፤

፮. የጦር ሠፈሮችንና ለሠራዊቱ የሚያስፈልጉትን የመኖሪያ ሠፈሮች ይሠራል፣ ያሠራል፤

፯. የአገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦችን ሚዛናዊ ተዋጽዖ ያካተተ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፰. ተግባሩን ለሕገ-መንግሥቱ ተገዢ እና ከፖለቲካ ድርጅት ወገናዊነት ነፃ በሆነ አኳኋን ማከናወኑን ያረጋግጣል፤

፱. ከክልል አቅም በላይ የሆነ የፀጥታ መደፍረስ ሲያጋጥም በክልሉ መስተዳድር ጥያቄ መሠረት ሰላምና መረጋጋትን ያሰፍናል፤

፲. ማንኛውም ክልል ሕገ-መንግሥቱን በመጣስ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ ሲጥልና በሕገ-መንግሥቱ በተደነገገው መሠረት ሲታዘዝ ፀጥታንና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ያስከብራል፤

፲፩. የክተት አዋጅ በሚታወጅበት ጊዜ በአገር ውስጥ የሚገኝ ሀብት በተቀናጀ ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ዘዴ እያጠና ያስወስናል፤ ኅብረተሰቡ ከጠላት ጥቃት ራሱን የሚከላከልበትን ዕቅድ ያወጣል፣ ሲፈቀድም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፲፪. በጦርነት ወይም በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመከላከያ ሠራዊትን የሚቀላቀል፣ እንዲሁም ሰው ሠራሽም ሆነ የተፈጥሮ አደጋዎች ሲከሰቱ ዕገዛ የሚያደርግ ብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ይመለምላል፣ ያሰለጥናል፣ ያደራጃል፤

፲፫. አገሪቱ የሚቀርብላትን ዓለም አቀፍ የሰላም ማስከበር ጥሪ በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል የሰላም አስከባሪ ኃይል ያደራጃል፣ ያሰማራል፤

፲፬. የሠራዊቱ አባላት በሰላም ጊዜ በአገሪቱ የልማት ሥራዎች እንዲሳተፉ ያደርጋል፤

፲፭. ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኘውን ገቢ የሚኒስትሮች ምክር ቤትን እያስፈቀደ ለአገር መከላከያ አቅም ግንባታ እንዲውል ያደርጋል፡-

3. undertake responsibilities assigned to it under state of emergency proclamations;
4. establish, equip and supervise defense forces, and ensure their combat capabilities;
5. cause to the organization of defense forces training centers;
6. construct and cause the construction of military camps and residential quarters required for the defense forces;
7. ensure that the composition of the National Defense Forces reflect equitable representation of nations, nationalities and peoples;
8. ensure that it carries out its functions in accordance with the Constitution and free of any partisanship to any political organization;
9. enforce security measures upon request by Regional States where security situations that are beyond their control occur;
10. when commanded in accordance with the Constitution, enforce security and constitutional order where any Regional State violates the Constitution and endangers the constitutional order;
11. in the event of declaration of national mobilization, prepare plans and get authorizations for the coordinated utilization of resources in the country; prepare schemes whereby the public can defend or guard itself against enemy threats, and, upon authorization, implement same in cooperation with concerned organs;
12. recruit, train and organize a national reserve force that shall join the armed forces in time of war or state of emergency and that shall provide assistance in the event of man-made or natural disasters;
13. organize and deploy competent peace keeping forces where the country is required to participate in international peace keeping missions፤
14. ensure that the defense forces participate in the country's development activities in times of peace;
15. retain and utilize income derived from the following sources for national defense capacity building upon obtaining the approval of the Council of Ministers:

ሀ) የመከላከያ ተቋማት በሰላም ጊዜ የሚኖራቸውን የማምረትና አገልግሎት የመስጠት ትርፍ አቅም ለገቢ ማስገኛ ተግባር እንዲውል በማድረግ የሚገኘውን ገቢ፤

ለ) ለመከላከያ ጠቀሜታ የማያስፈልጉ ንብረቶችን በማስወገድ የሚገኘውን ገቢ፤ እና

ሐ) በተቆጣጣሪ ባለሥልጣንነት ከሚመራቸው ድርጅቶች የሚገኘውን የትርፍ ድርሻ፤

፲፮. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፲፭ የተመለከተው ገንዘብ አስተዳደር በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፰/፪ሺ፩ እና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተደነገጉትን ሥርዓቶችና መመዘኛዎች ተከትሎ መፈጸሙን ያረጋግጣል፣ በዋናው ኦዲተርም እንዲመረመር ያደርጋል።

**፲፭. <u>የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር</u>**

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የኢትዮጵያን ሕዝቦች ጥቅም የሚያስጠብቅ፣ የአገሪቱን ሉዓላዊነት የሚያስከብር፣ በጋራ ጥቅምና እኩልነት ላይ የተመሰረተ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ይቀርጻል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም በሥራ ላይ ያውላል፤

፪. አገሪቱ ባላት የውጭ ግንኙነት ጥቅሟና መብቷ እንዲጠበቅና በሌሎች መንግሥታት እንዲከበር ያደርጋል፤ አገሪቱ ከጎረቤት አገሮች ጋር ያላት መልካም ጉርብትና እንዲጠናከር ያደርጋል፤

፫. ሥልጣኑ በተለይ ለሌላ አካል በሕግ ካልተሰጠ በስተቀር፣ ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግሥታትና ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር የምታደርጋቸውን በመንግሥት የተፈቀዱ ዓለም አቀፍ ውሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ይደራደራል፣ ይፈርማል፤ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ውሎች እንዲፀድቁ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ፎርማሊቲዎች ሁሉ ያከናውናል፤

፬. ሌሎች የመንግሥት አካላት ከውጭ አገር መንግሥታትና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የሚያደርጓቸውን ሁሉንም ግንኙነቶች ያስተባብራል፤

፭. ሥልጣኑ በተለይ ለሌላ አካል ካልተሰጠ በስተቀር፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የፈረማቸው ዓለም አቀፍ ውሎች የሚያስከትሏቸው መብቶችና ግዴታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

a. revenue generated by employing idle facilities of defense institutions in times of peace in income generating activities;

b. the proceeds of disposal of properties which are no more required for defense purposes; and

c. dividends from enterprises put underits supervision

16. ensure that the administration of the fund referred to in sub-article 15 of this Article is carried out according to the procedures and standards embodied in the Financial Administration Proclamation No. 648/2009 and, regulations and directives issued pursuant to the proclamation, and submit same for auditing by the Auditor General.

**15. <u>Ministry of Foreign Affairs</u>**

The Ministry of Foreign Affairs shall have the powers and duties to:

1. formulate foreign policy based on the principle of mutual respect and equality that protects the interests of the people of Ethiopia and safeguard its sovereignty, and implement same upon approval;
2. safe guard the interests and rights of the country in connection with its foreign relations and ensure that they are respected by foreign states; ensure that the country’s good relations with neighboring countries are strengthened;
3. except in so far as such power is specifically given by law to other organs, in consultation with relevant organs, negotiate and sign, upon approval by the government, treaties that Ethiopia enters into with other states and international organizations; and effect all formalities of ratification of treaties;
4. coordinate all relations of other government organs with foreign states and international organizations;
5. ensure the enforcement of rights and obligations arising from treaties signed by the Governmentof Ethiopia except in so far as specific power has legally been entrusted to other organs;

፮. ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግሥታትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የምታደርጋቸውን ዓለም አቀፍ ውሎች ሁሉንም የተመሰከረላቸውን ዋናዎቹን ቅጂዎች መዝግቦ ይጠብቃል፤

፯. የኢትዮጵያ መንግሥት በብዙ መንግሥታት መካከል የሚደረጉ ዓለም አቀፍ ውሎችን አስቀማጭ በሚሆንበት ጊዜ ይኸው ባለአደራነት የሚጠይቀውን ተግባር ያከናውናል፤

፰. በኢትዮጵያ ከሚገኙ የውጭ ሃገራት መንግሥታት እንደራሴዎች፣ ቆንስሎችና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወኪሎች ጋር እንደአስፈላጊነቱ በመገናኘት የጋራ ጥቅሞች የሚጠበቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፱. በዓለም አቀፍ ሕግና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ውሎች ለውጭ አገር መንግሥታት እንደራሴዎችና ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወኪሎች የተሰጡ መብቶች እንዲከበሩ ያደርጋል፤

፲. በውጭ አገር የኢትዮጵያ የዲፕሎማቲክና የቆንስላ ሚስዮኖችን እንዲሁም በዓለም አቀፍ ድርጅቶች የኢትዮጵያ ቋሚ መልእክተኞች ጽሕፈት ቤቶችን ተግባራት ያስተባብራል፣ ሥራቸውንም ይቆጣጠራል፤

፲፩. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ ፓስፖርቶች እና የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ መግቢያ ቪዛዎች ይሰጣል፤

፲፪. የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ በማካሄድ:-

ሀ) የአገሪቱን የውጭ ንግድና ቱሪዝም ለማስፋፋት፣

ለ) የውጭ ኢንቨስተሮችን ለመለየትና ለመሳብ፣

ሐ) ቴክኖሎጂን ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ እና ለማስገባት፣

መ) የውጭ የልማት ፋይናንስና የቴክኒክ ተራድዖ የሚገኝበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣

ለሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ ይሠጣል፤

፲፫. በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መብትና ጥቅም እንዲጠበቅ ያደርጋል፤ በኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብና በኢትዮጵያ ወዳጆች የተመሠረቱ ማኅበራትን ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፬. የዳያስፖራ ተሳትፎን በማረጋገጥ ዲያስፖራው በአገር ልማት እንዲሳተፍ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፲፭. በፕሮቶኮል ጉዳዮች ላይ መረጃዎችንና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

6. register and keep all authentic copies of treaties concluded between Ethiopia and other states and international organizations;

7. perform the functions of a depository of multi lateral treaties when the Government of Ethiopia is adepository of such treaties;

8. maintain contacts, as may be necessary,with foreign diplomatic and consular representatives in Ethiopia as well as with representatives of international organizations with a view to facilitating the protection of mutual interests;

9. ensure that privileges and immunities accorded to foreign diplomatic missions and representatives of international organizations under international law and treaties to which Ethiopia is aparty are respected;

10. coordinate andsupervisetheactivities of Ethiopia’s diplomatic and consular missions abroad and permanent missions offices in international organizations;

11. issue diplomatic and service passports and diplomatic and service entry visas in accordance with the relevant laws;

12. provide support to relevant organs by pursuing economic diplomacy to:

a. promote the country's foreign trade and tourism;

b. identify and attract foreign investors;

c. search, choose and cause the transfer of technology;

d. facilitate the mobilization of financial and technical assistance from external sources;

13. ensure that the interests and the rights of Ethiopians residing abroad are protected; encourage and support associations formed by Ethiopian communities and friends of Ethiopia;

14. facilitate participation of the diasporas in the development of the country through ensuring diaspora engagement;

15. provide information and advice on issues of protocol;

፲፮. በፐብሊክ ዲፕሎማሲና ኮሙኒኬሽን ተግባራት የአገር ገጽታን የመገንባትና ደጋፊዎችን የማበራከት ስልቶችን ይነድፋል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል።

## ፲፮. የገንዘብ ሚኒስቴር

፩. የገንዘብ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

ሀ) የኢኮኖሚ ትብብርና የፊስካል ፖሊሲዎችን በተለይም ለታክስና ለቀረጥ ሕጎች መሠረት የሚሆኑ ፖሊሲዎችን ይቀርጻል፣ በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ የማሻሻያ ሀሳቦች ያመነጫል፤

ለ) ከተለያዩ መንግሥታት ጋር የሚደረገውን የሁለትዮሽ ኢኮኖሚ ትብብር እንዲሁም የኢኮኖሚ ትስስር ለመፍጠር ከተቋቋሙ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ጋር የሚደረገውን ግንኙነት ይመራል፣ ያስተባብራል ፤ የዚህ ዓይነቱ ትስስር በአገሪቱ የኢኮኖሚ አፈጻጸም ላይ የሚኖረውን ውጤት ይከታተላል፤

ሐ) የውጭ ዕርዳታና ብድር ያሰባስባል፣ ይደራደራል፣ ይፈርማል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

መ) የፌደራል መንግሥት አክሲዮኖችን፣ የሚተላለፉና የማይተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችንና ሌሎች ተመሳሳይ ተቀማጭ የገንዘብ ሀብቶችን ይይዛል፣ ይጠብቃል፤

ሠ) የፌደራል መንግሥቱን በጀት ያዘጋጃል፣ በተፈቀደው በጀት መሠረት ክፍያ ይፈጽማል፣ የበጀቱን አፈጻጸም ይገመግማል፤

ረ) የፌደራል መንግሥቱን የግዢና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

ሰ) የፌደራል መንግሥትን የበጀት፣ የሂሣብ አያያዝ፣ የክፍያና የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ይዘረጋል፣ የአፈጻጸሙን ውጤታማነት ይከታተላል፤ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀና አንድ ወጥ የፌደራልና የክልል መንግሥታት የበጀት፣ የሂሣብ አያያዝ፣ የክፍያና የውስጥ ኦዲት ሥርዓቶች የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

16. design and follow up the implementation of public diplomacy and communication strategies to build the country's image and to rally supporters.

## 16. Ministry of Finance

1. The Ministry of Finance shall have the powers and duties to:

a. formulate economic cooperation and fiscal policies that particularly serve as a basis for taxes, and duties; follow up the proper implementation of same; initiate reform recommendations;

b. lead and coordinate bilateral economic cooperation with other countries as well as the relationship with international and regional organizations set up to create economic cooperation; follow up the impact of such links on the performance of the country's economy;

c. mobilize, negotiate and sign foreign development assistance and loans, and follow up the implementation of same;

d. be the depository of and safe guard the Federal Government's shares, negotiable and non-negotiable instruments and other similar financial assets;

e. prepare the Federal Government fiscal budget ,make disbursements in accordance with the approved budget, and evaluate the utilization of the budget;

f. establish procurement and property management system of the Federal Government and supervise the implementation of same;

g. establish budgeting, accounting, dis bursement and internal audit systems for the Federal Government, and follow up the effectiveness of the implementation of same; ensure the implementation of systems of budgeting, accounting, dis bursement and internal audit that are harmonized and aligned with international standards at the levels of both federal and regional governments;

ሸ) የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ፕራይቬታይዝ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ያዘጋጃል፤ ከሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት ጋር በመቀናጀት የፕራይቬታይዜሽን ሂደቱን ያሳልጣል።

፪. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎችና ድንጋጌዎች ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለገንዘብ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## ፲፯. ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ

በአዋጅ ቁጥር ፱፻፵፫/፪ሺ፰ መሰረት ለፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ፡-

፩. በፌደራል ፖሊስ ምርመራ ዘርፍ የሚከናወኑ የምርመራ ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤

፪. በምርመራ ሥራ ላይ የተሰማሩ መርማሪዎችና ኃላፊዎችን የሥራ ስምሪት ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤ የሥራ ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፤

፫. ከፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ጋር በመመካከር የመርማሪዎችና የምርመራ ክፍል ኃላፊዎች የደመወዝና ጥቅማጥቅም ሁኔታን በማጥናት እንዲወሰን ያደርጋል።

## ፲፰. የግብርና ሚኒስቴር

፩. የግብርና ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የገጠር መሬት አስተዳደርና ለተፈጥሮ ግጦሽ መሬት ዘላቂ የአጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋቱን ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ አገራዊ መረጃ ያደራጃል፤

ለ) ለአርሶ አደሮች፣ ለአርብቶ አደሮችና፣ ከፊል አርብቶ አደሮች ተደራሽ የሆነ የገጠር ፋይናንስ ሥርዓት እንዲዘረጋ ለሚመለከታቸው የፋይናንስ አካላት ያመቻቻል፤

ሐ) የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ውሃን ማዕከል ያደረጉ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ የተፈጥሮ እና የመስኖ ግጦሽ መሬት ልማት እና አጠቃቀም ሥርዓት ይዘረጋል፣ የአነስተኛ መስኖ ልማቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

መ) የግብርና ልማትን ለማፋጠንና የገጠር ቴክኖሎጂን ለማሻሻል የሚረዱ የማሰልጠኛ ማዕከሎችን ያቋቁማል፣ይመራል፤

h. prepare documents needed to privatize public enterprises; facilitates privatization processes in collaboration with relevant government bodies.

2. The powers and duties given to the Ministry of Finance and Economic Cooperation by the provisions of other laws currently in force are hereby vested in the Ministry of Finance.

## 17. The Attorney General

The Attorney General shall, in addition to the powers and duties given to it by the Federal Attorney General Establishment Proclamation No. 943/2016:

1. lead, supervise, follow up and coordinate the criminal investigation function of the Federal Police;
2. assign investigators and 'lead-investigators' with work assignments; supervise the same; cause progress report to be submitted to it;
3. in consultation with the Federal Police, conduct or commission a study on the salary and benefits situation of investigators and 'lead-investigators';

## 18. Ministry of Agriculture

1. The Ministry of Agriculture shall have the powers and duties to:
   a. follow up and provide support for the establishment of rural land management and sustainable grazing land utilization systems ; organize a national data base on same;
   b. facilitate the establishment of accessible rural finance system by the relevant finance institutions to farmers, pastoralists, and semi-pastoralists;
   c. foster basin developments on water bodies in pastoral and semi-pastoral areas; establish natural and irrigated pasture utilization system; foster small-scale irrigation developments;
   d. establish and run training centers that assist to the enhancement of agricultural development and the improvement of rural technologies;

ሠ) በገጠር የምግብ ዋስትና እና የሥራ ዕድል ፈጠራን የሚመለከቱ ተግባራትን ያስተባብራል፤

ረ) በአርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት ሀብት ልማት አስፈላጊ የሆኑ የውሃ ተፋሰስ ሥራዎች፣ መሠረተ ልማትና የመኖ ባንኮች መስፋፋታቸውን ይከታተላል፤

ሰ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የከተማ ግብርናን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል ስልት ይነድፋል፣ የአተገባበር ሥርዓት ይዘረጋል፤

ሸ) የሰብል፣ እንስሳትና የዓሣ ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል፣ የምርት ጥራት ለማሳደግና ብክነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ውጤታማ ቴክኖሎጂዎች፣ የግብርና ኤክስቴንሽን፣ የሥልጠና፣ የአቅም ግንባታ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

ቀ) ብሔራዊ የእንስሳት ርቢ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ፕሮግራም ይቀይሳል፤

በ) የእንስሳትና ዓሣ ጤና አገልግሎትን ጥራትና ተደራሽነት ለማሻሻል፣ በሽታን ለመከላከልና ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤ በአገር ውስጥ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎች እንዲገነቡ ያደርጋል፣ አቅማቸውን ይገነባል፤

ተ) በሰብል ምርት፣ በእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ላይ ተፅዕኖ ለሚያስከትሉ ወቅታዊ ሁኔታዎች የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ይዘረጋል፣

ቸ) የሰብል ምርት፣ የእንስሳትና ዓሣ ግብዓት አቅርቦት፣ ሥርጭትና ግብይት አቅምን በመገንባት አስተማማኝ አቅርቦትን ያረጋግጣል፤ የጥራት ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ የገበያ ትስስር በመፍጠር አቅርቦትን ለማሻሻል የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፤

ኀ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለገበያ የሚቀርብ ማንኛውም የሰብል ምርት፣ እንስሳ፣ ዓሣ፣ የእንስሳትና ዓሣ ምርትና ተዋጽዖ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ዘመናዊ አመራረት እንዲጎለብትና የገበያ ትስስር እንዲፈጠር የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፣

e. coordinate activities relating to food security and job creation schemes;

f. follow up the expansion of basin developments, infrastructure and fodder banks necessary for livestock develop ment;

g. in collaboration with the relevant organs, formulate techniques for a successful urban agriculture, and a procedure for their implementation;

h. promote the expansion of effective technologies, agricultural extension, trainings, and capacity building services that help to improve production and productivity and quality of crops, livestock and fishery, and reduce wastages;

i. formulate national livestock breeding policy, strategy and program;

j. establish a system that ensures access to quality veterinary services to improve the prevention and timely control of animal and fish diseases; cause the building of animal health laboratories in the country and build their capacity;

k. establish early warning system in respect of current situations that affect crop production, and livestock and fishery development;

l. build capacity for supplying, distributing, and marketing of inputs for crop production, livestock and fishery development in order to ensure reliable supply of produce; establish and follow up the implementation of a quality control system; provide technical support to improve supply of products through the creation of market linkage;

m. establish a system to ensure that all crop, livestock, fish, livestock and fish products marketed maintain the required quality; follow up the implementation of such system; provide technical support to create modern production systems and market linkages;

ነ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውጤታማ ቅንጅት በመፍጠር የግብርና ኢንቨስትመንትን የሚመለከቱ ሥራዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤ ሰፋፊ የግብርና ኢንቨስትመንት ሥራዎች የሚስፋፉበትን ስልት ይቀይሳል፤

ኘ) የግብርናና ኢንዱስትሪውን ትስስር ለማጠናከር ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል መንግሥት አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፤

አ) የሰብል ምርትና የእንስሳት ልማት ምርምር ባለድርሻ አካላት በቅንጅትና በትብብር የሚሰሩበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤

ከ) የጸረ-ተባይ ኬሚካሎች፣ የእንስሳት መድኃኒቶች ፣መኖ ጥራትና የእንስሳት ሕክምና አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራዎች በአግባቡ መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤

ኸ) የእጽዋትና የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከልና ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለዚህ የሚያስፈልገውን ጥናትና ምርምር ይመራል፤ ወደ አገር በሚገቡትም ሆነ ከአገር በሚወጡት እጽዋትና አዝዕርት፣ እንስሳትና የእንስሳት ተዋጽዖዎች ላይ የኳራንቲን ቁጥጥር ያደርጋል፤

ወ) የቡና እና የሻይ ልማት እና ግብይት የሚመለከቱ ሥራዎች በአግባቡ መተግበራቸውን ያረጋግጣል፤

ዐ) የግብርና የኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

ዘ) የአፈር መሸርሸር መንስኤዎችን በመለየት የመከላከያ ስልቶች ተነድፈው ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ የአፈር ለምነት የሚሻሻልበትን፣ የአፈር ጤና የሚጠበቅበትን እና አገራዊ የአፈር መረጃ ሥርዓት የሚዘረጋበትን ስልት ይነድፋል፤

ዠ) የተፈጥሮ ሀብት በዘላቂነት እንዲለማና እንዲጠበቅ፣ የጥምር እርሻ ቴክኖሎጂ እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

የ) የድርቅ ተጋላጭነትን ለማስወገድ የሚያስችሉ ተግባራትን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያስተባብራል፤

ገ) በግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፍ የተሰማሩ ኩባንያዎች የሚያስፈልጋቸውን ሰርቲፊኬቶች የሚሰጥበትን አግባብ ይወስናል።

n. by creating effective collaboration with the relevant organs, ensure that agricultural investment activities are undertaken properly; devise strategy to promote large agricultural investments;

o. work in coordination with relevant Federal Government and Regional State bodies to strengthen the linkage between agriculture and industry;

p. develop a system that ensures integration and coordination of stake holders engaged in crop production and livestock develop ment research;

q. ensure the proper execution of pesticide and animal feed quality control, and veterinary administration and regulatory activities;

r. establish a system that enables the prevention of plant and animal diseases; lead research and studies necessary to this end; conduct disease-control activities in respect of plants, cereals, animals and animal products crossing Ethiopia's border;

s. ensure the proper execution of functions relating to coffee and tea development and marketing activities;

t. promote the expansion and strengthening of agricultural cooperatives;

u. establish a mechanism for the implementation of soil erosion prevention strategies by identifying its causes; design mechanisms for the improvement of soil fertility, protection of soil health, and for establishing national soil database;

v. cause the expansion of integrated farming to ensure sustainable development and maintenance of natural resources;

w. coordinate, in collaboration with concerned organs, activities that enable to mitigate drought vulnerability;

x. Determine conditions for the issuance of certificates that may be required by companies engaged in agricultural investment

፪. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎችና ድንጋጌዎች ለግብርናና እንስሳት ሃብት ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለግብርና ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

**፲፱. የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር**

፩. የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

ሀ) የንግድና ኢንዱስትሪ ልማትና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን ይቀርጻል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ) የግል ዘርፉን ተሳትፎ ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፣

ሐ) የአገር ውስጥ ንግድ እንዲስፋፋና ሕጋዊ አሠራር እንዲሰፍን ተገቢነት ያላቸውን እርምጃዎች ይወስዳል፤ በክልሎች መካከል የሚደረግን የንግድ ግንኙነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

መ) የአገሪቱ የወጪ ንግድ የሚስፋፋበትና የሚጠናከርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ሠ) በአገልግሎት፣ በግብርናና፣ በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሠማሩ የአገር ውስጥ ባለሃብቶች ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ ከሌሎች ተቋማት ጋር በመቀናጀት አስፈላጊውን ድጋፍ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ረ) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የውጭ ንግድ ግንኙነቶችን ይመሠርታል፣ የንግድ ስምምነቶችን በሕግ መሠረት ይፈራረማል፣ ያስፈጽማል፤

ሰ) የወጪና ገቢ ንግድ ዕቃዎችን ጥራት ይቆጣጠራል፣ ተፈላጊውን የደረጃ መሥፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከአገር እንዳይወጡ ይቆጣጠራል፤

ሸ) የወጪና ገቢ ዕቃዎች በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸው ወይም ስለመገዛታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ክትትል ያደርጋል፤

ቀ) ቀላል፣ ወጪ ቆጣቢና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ሥርዓት ይዘረጋል፤

2. The powers and duties given to the Ministry of Agriculture and Livestock Resources by the provisions of other laws currently in force are hereby vested in the Ministry of Agriculture.

**19. The Ministry of Trade and Industry**

1. The Ministry of Trade and Industry shall have the powers and duties to:

a) formulate policies that ensure sustained development and sustained competitive ness in trade and industry, and implement same upon approval by the pertinent body;

b) create an enabling system for increased participation of the private sector; facilitate the implementation of same;

c) promote the expansion of domestic trade and take appropriate measures to maintain lawful trade practices; lead and oversee trade relations between Regional States;

d) create conducive environment for the expansion and promotion of the country’s export trade;

e) establish system, in coordination with other agencies, for the provision of support to domestic investors engaged in service, agriculture and industrial sector in exporting their produces to overseas markets; and implement same;

f) in collaboration with relevant bodies, establish foreign trade relations, sign trade agreements in accordance with the law, and oversee implementation of same;

g) control the qualities of export and import goods; prohibit the importation or exportation of goods that do not conform with the required standards;

h) establish system to ascertain that export or import goods are traded or bought at appropriate prices; follow up same in collaboration with concerned agencies;

i) provide simple, cost effective and technology supported commercial registrationand business licensing services;

በ) የዋጋ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ዋጋ እያጠና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

ተ) የንግድና የዘርፍ ማኅበራት፣ የሸማቾች ማኅበራት፣ የኢንዱስትሪ፣ የዘርፍና የሙያ ማኅበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፤የተቋቋሙ ትንም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

ቸ) የአገሪቱን ሕጋዊ ሥነ-ልክ ሥርዓት ለመተግበር እንዲቻል አስፈጻሚ አካላትን ያስተባብራል፤

ኀ) አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን ይቆጣጠራል፣ በሌሎች አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች የሚሠራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበሩ ያደርጋል፣

ነ) የኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችንና መርሃ ግብሮችን ያዘጋጃል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቁም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ኘ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ስትራቴጂካዊ ትኩረት በሚሰጣቸው ዘርፎች የአገሪቱን ምርቶች ለውጭ ገበያ በማቅረብ ረገድ የታቀደውን ዕድገት ለማምጣት የሚያስፈልጉ ጥናትና ምርምሮች ያካሂዳል፣ ይተገብራል፤

አ) በኢንቨስትመንት አዋጁ መሠረት የአገር ውስጥ ባለሃብቶች በኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት የሚሳተፉበትን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤ በሥሩ ያሉ ተጠሪ ተቋማት በዋናነት ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ድጋፍ እንዲሰጡ ለማድረግ ተገቢውን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈጽማል፤

ከ) የኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትን ለማሳደግ የሚያስችል የቴክኖሎጂ መረጣ፣ ማላመድና ማስረጽ ተግባራትን፤ የምርጥ ተሞክሮ መቀመር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የክህሎት ልማት እና አጠቃላይ የኢንዱስትሪ ልማት አቅም ግንባታ ሥራዎችን ያመቻቻል፤

j) undertake and submit to the Council of Ministers studies relating to prices of basic commodities and services that require price control; oversee implementation of same upon approval;

k) encourage the establishment of chambers of commerce and sectoral associations, consumers'associations, industry, sectoral and professional associations, and strengthen those which are already operational;

l) coordinate the concerned enforcement bodies for the implementation of the legal metrological system of the country;

m) control the compliance of goods with the requirements of mandatory Ethiopian standards, and take measure against those found to be below the standards set for them; cause the coordinated enforcement of standards applied by other enforcement bodies;

n) design policies, strategies and plans that help in fast-tracking industrial development; implement same upon approval by the concerned body;

o) conduct studies and researches to facilitate the realization of plans that enhance export in industries having strategic importance; and implement same in collaboration with the relevant agencies;

p) in accordance with investment laws, create conducive environment for the participation of domestic investors in industrial development and establish system for the provision of appropriate support; establish systems to enable the institutions accountable to it to support domestic investors; and implement the same;

q) facilitate the selection, adoption and inculcation of technology that accelerates industrial sector development; expedite the acquisition of best practices, technology transfer and skills development and general capacity building activities in industrial development;

ኸ) የኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትና ምርታማነትን ለማሳደግ ኢንዱስትሪዎች የኤክስቴሽን አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂ፣ የግብዓትና የግብይት እንዲሁም በአመራረት ረገድ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ውጤታማነታቸውንም ያረጋግጣል፤

ወ) የኢንዱስትሪ ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የአቅም ግንባታ፣ የምርምርና ስርጸት ሥራዎች እንዲከናወኑ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

ዐ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለኢንዱስትሪ ዘርፍ አስፈላጊ የሆነው የሰው ኃይል ፍላጎት እና አስተማማኝ ግብዓት ለማሟላት የሚያስችልበትን ስልት ይቀይሳል፤

ዘ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሥራት የግብዓት አቅርቦት ትስስር ሥርዓት እንዲዘረጋ ሁኔታዎች ያመቻቻል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ዠ) ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታቸው ጉልህ የሆኑ ገቢ ምርቶችን በአገር ውስጥ ምርቶች እንዲተኩ ድጋፍ ያደርጋል፤ ገበያው ሊያቀርባቸው ያልቻለው ወይም እጥረት በሚታይባቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ዘርፍ መንግስት የሚያቀርብበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

የ) በአነስተኛ፣በመካከለኛና በከፍተኛ ኢንዱስትሪ ዎች መካከል የተቀናጀ ትስስር እንዲፈጠርና ስኬታማ ሽግግሮች እንዲከናወኑ የሚያስችሉ የአሠራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤

ገ) ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ ጥበቃ የተቀመጡ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ድጋፍ ያደርጋል፤

ደ) የአገሪቱን የንግድና ኢንዱስትሪ መረጃዎች አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና አጠቃቀምን ያስተባብራል፣ የተቀናጀ መረጃ ያደራጃል፤ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤

፪. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎችና ድንጋጌዎች ለንግድ ሚኒስቴር እና ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## ፳. <u>የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር</u>

፩. የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

r) cause the provision of assistance including industrial extension services, technology, inputs, marketing and manufacturing methods and thereby ensure growth and productivity of the industrial sector; and monitor the effectiveness thereof;

s) establish systems of capacity building, research and inculcation to maintain quality standards and competitiveness of industrial products in international markets; oversee implementation of the same;

t) design mechanisms to meet human resources and sustainable input provisions required in the industrial sector;

u) work in cooperation with concerned bodies to create conditions necessary for the establishment of system for industrial input provision linkages, and implement the same;

v) extend support to substitute import goods having strategic importance with local production; create necessary conditions for government provision of goods and services which are not supplied by the market system or are in short provisions;

w) develop working mechanisms to create linkage between small, medium and large-scale industries and facilitate effective transformation;

x) provide support to industries so as to ensure compliance with environmental protection requirements;

y) coordinate the collection, organization and utilization of national trade and industry data; maintain organized information system; and disseminate same to pertinent bodies;

2. The powers and duties given to the Ministry of Trade and the Ministry of Industry by provisions of other laws currently in force are hereby vested in the Ministry of Trade and Industry.

## 20. <u>The Ministry of Innovation and Technology</u>

1. The Ministry of Innovation and Technology shall have the powers and duties to:

ሀ) የአገሪቱን የልማት አቅጣጫ መሠረት ያደረገ አገራዊ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ያስፈጽማል፤ በብቃት ለማስፈጸም የሚያስችል ተቋማዊ አቅም እና የሰው ኃይል ልማት ያቅዳል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

ለ) ለክልሎች ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ተቋማት አቅም ግንባታ አስፈላጊውን የሙያና ቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

ሐ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎቶች ጥራታቸው፣ ደህንነታቸውና አስተማማኝነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን የሚያስችሉ ደረጃዎችን ይወስናል፣ተግባራዊመደረጋቸውን ይቆጣጠራል፤

መ) በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ተቋማትና ባለሙያዎች አቅም ግንባታን ይደግፋል፤ የሙያ ማኅበራትንና አካዳሚዎችን ይደግፋል፣ ያበረታታል፤

ሠ) የአገሪቱ ሥርዓተ-ትምህርት ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት አንፃር መቃኘቱን ለማረጋገጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይተባበራል፤

ረ) የቴክኖሎጂ ፍላጎት ለመዳሰስ፣ ተገቢ ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግና በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ሥርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

ሰ) ለአገሪቱ ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ አዳዲስ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ የጥናትና ምርምር መስኮችን ይለያል፤ አገራዊ የምርምር ፕሮግራሞችን ያስተባብራል፤

ሸ) አገር-በቀል ቴክኖሎጂዎችን ለማሻሻል፣ ለማሳደግና ለገበያ ለማቅረብ የሚደረጉ ጥናቶችን፣ የምርምርና ስርጸት ሥራዎችን ያበረታታል፣ ወደተግባር እንዲሸጋገሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤ ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ መዳበር የበለጠ አስተዋጽዖ ሊያደርጉ የሚችሉ ግለሰቦችን፣ የሙያ ማኅበራትንና አካዳሚዎችን ያበረታታል፣ ይደግፋል፤

ቀ) ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማትና ለፈጠራ ሥራዎች ዕድገት አስተዋጽዖ ላበረከቱ ግለሰቦችና ተቋማት ሽልማትና ማበረታቻ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፤

a) prepare national innovation and technology research and development programs based on the country's development priorities; plan institutional capacity and human resources development for effective implementation of the programs; and follow up the same;

b) provide professional and technical support to regions' innovation and technology institutions;

c) in collaboration with relevant bodies, set standards to ensure the provision of quality, reliable and secure information technology services, and oversee implementation thereof ;

d) support capacity building of institutions and professionals involved in innovation and technology activities; support and encourage professional associations and academies;

e) collaborate with pertinent bodies to ensure that the country's educational curricula are designed in tune with innovation and technology development;

f) prepare and oversee the implementation of system for the identification, exploration and application of appropriate technologies in collaboration with the pertinent bodies;

g) identify new innovation and technology studies and research areas pertinent to the country's development; coordinate national research programs on the same;

h) support studies, researches and dissemination works for the enhancement, development and marketing of indigenous technologies; assist such works to advance their practical application; encourage and support individuals, professional associations and academies particularly involved in strengthening innovations and technologies;

i) establish and implement system for the grant of awards and incentives to individuals and institutions contributing to the advancement of innovation and technological development works;

በ) በየዘርፉ በሽግግር የሚመጡ ቴክኖሎጂዎችን መረጃ ይመዘግባል፣ ኮዲፋይ የማድረግና የማቀብ ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ለቀጣዩ ሥራ እንቅስቃሴም እንዲውሉ ያደርጋል፤

ተ) ለሕዝብ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያተኮሩ መሠረታዊ ሲስተሞችና አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ የተደገፉ እንዲሆኑና ለተጠቃሚዎች የተሻለ አገልግሎት ሊሰጡ በሚችሉበት ሁኔታ መመቻቸታቸውን ያረጋግጣል፤

ቸ) የምርምር ሥራዎችን ለማስተባበር የሚያግዙ ምክር ቤቶችን ያቋቁማል፣ ያስተባብራል፣ ይደግፋል፤

ኀ) የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ መረጃ ቋት ያደራጃል፣ መረጃዎችን ያጠናቅራል፤ አገራዊ የመረጃ አያያዝ ደረጃ ያወጣል፤

ነ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የፌደራልና የክልል መንግሥታዊ ተቋማት የመረጃ ሥርዓትን ይገነባል፣ ያቀናጃል፤ ደህንነቱ የተጠበቀ የኢንፎርሜሽን መረብ የመዘርጋት ሥራን ይደግፋል፤

ኘ) የአገሪቱን ከፍተኛ ደረጃ መለያ ዶሜይን ስም አገራዊ የአስተዳደር ሥርዓት እንዲፈጠርና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል የሚመለከታቸውን ያስተባብራል፣ ይከተታተላል፤ በመንግሥታዊ ተቋማት የመረጃ ሥርዓትን ለመገንባትና ለማቀናጀት የዶሜይን ስም ይደለድላል፣ አድራሻ ይመዘግባል፣ይቆጣጠራል፤

አ) የጨረራና ጨረር አመንጪ ቁሶች አጠቃቀምና አወጋገድ ቁጥጥር ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፤

ከ) ብሔራዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር ፕላን ያወጣል፣ ቁጥሮችን ይመድባል፣ ያስተዳድራል፣ አጠቃቀማቸውን ይቆጣጠራል፤

ኸ) የቴሌኮሙኒኬሽንና የፖስታ አገልግሎቶች በመስጠት ሥራ ላይ ለሚሰማሩ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤ የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎችን የቴክኒክ ብቃት ያረጋግጣል፤

ወ) ለኢትዮጵያ የተመደበውን የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ አጠቃቀም ይፈቅዳል፣ ይቆጣጠራል።

፪. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎችና ድንጋጌዎች ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በተመለከተ ለመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት፤ ቴክኖሎጂን በተመለከተ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት

j) coordinate the registration, codification and conservation of technologies attained acquired through transfers across sectors; and ensure their subsequent utilization;

k) ensure that mission critical systems and services in public sector are supported by appropriate technology and positioned to better provide services to the public;

l) establish, coordinate and support councils that facilitate the coordination of research works;

m) organize innovation and technology data base, compile information, set national standards for information management;

n) in collaboration with relevant bodies, support the development, deployment and coordination of secure information network within federal and regional government institutions;

o) coordinate pertinent stakeholders for the creation and proper utilization of country code top level domain system; facilitate and oversee proper implementation of the same; assign and monitor government domain names and register addresses to develop and coordinate government institutions' information system;

p) prepare and implement system for regulating the utilization and disposal of radiation and radiation producing items;

q) establish national telecommunication numbering plan, assign and administer numbers, and supervise the efficient utilization thereof;

r) provide licenses and regulate telecommunication and postal service operators; ensure the technical quality of telecommunication equipment;

s) authorize and supervise the utilization of radio frequencies allotted to Ethiopia;

2. The powers and duties given by provisions of other laws currently in force to the Ministry of Communications and Information Technology in relation to matters pertaining to information technology and to the Ministry of Science and Technology in relation to

በዚህ አዋጅ ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## ፳፩. የትራንስፖርት ሚኒስቴር

የትራንስፖርት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የአገሪቱን የልማት ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ለማድረግ፣ የልማት ማዕከላትንና የዕድገት ኮሪደሮችን የትራንስፖርት ፍላጎት ለማሟላት የየብስ፣ የአየርና የባህር ትራንስፖርት አገልግሎቶች የተቀናጁ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

፪. የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶችን በተመለከተ አገራዊ ዕቅዶች ያወጣል፤ አስተማማኝና ደህንነታቸው የተረጋገጠ እንዲሆኑ የሚያስችሉ የቁጥጥር ሥርዓቶችን እንዲዘረጉና ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

፫. የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶች መዘርጋታቸውን፣ መስፋፋታቸውንና መጠገናቸውን ያረጋግጣል፤ የአጠቃቀም፣ የአያያዝና የአስተዳደር ደረጃዎችና ሥርዓቶችን ይወስናል፤ ተግባራዊነታቸውንም ያረጋግጣል፤

፬. በትራንስፖርት ዘርፉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና አሠራሮች በአገር ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ፣ እንዲስፋፉና እንዲዳብሩ ያደርጋል፤

፭. የትራንስፖርት መሠረተ-ልማቶችና አገልግሎቶች በአካባቢና አየር ንብረት የሚኖራቸውን ተፅዕኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ ስልቶችን በመለየት ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

፮. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ክልሎችን የሚያገናኙ አውራ መንገዶችን የማስፋፋትና የማስተዳደር ሥራን ያስተባብራል፤

፯. የትራንስፖርት ማኔጅመንት ሥርዓቱን ለማሻሻልና የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ችግርን በመሰረታዊነት ለመፍታት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያከናውናል፣ ይተገብራል፣

፰. የአውሮፕላን ትራንስፖርት አደጋ ምርመራ ተቀባይነት ባለው ደረጃ መሠረት መከናወኑን ያረጋግጣል፤

፱. የወጪና ገቢ ዕቃዎችን የተመለከቱ የትራንዚት ሥራዎችን ይቆጣጠራል፤ የአገሪቷ የሎጂስቲክስ ሥርዓት ቀልጣፋና ተወዳዳሪ መሆኑን ያረጋግጣል፤

matters pertaining to technology are hereby vested in the Ministry of Innovation and Technology.

## 21. The Ministry of Transport

The Ministry of Transport shall have the powers and duties to:

1) ensure the integration, efficiency and accessibility of land, air and sea transportation services, and thereby realize the country's development strategies and meet the transport service requirements of development hubs and corridors;
2) prepare national plans pertaining to the development of transport infrastructure; ensure the establishment and implementation of regulatory frameworks to guarantee the provision of reliable and safe transport services;
3) ensure that transport infrastructure are constructed, upgraded and maintained; set standards and systems to determine the usage, maintenance and administration of transport infrastructure; and ensure their implementation;
4) ensure the utilization, expansion and strengthening of advanced technologies and practices in the country's transport sector;
5) identify and implement measures that mitigate the impact of transport infrastructure and services on the environment and the climate;
6) expand, administer and control highways that connect two or more Regional States;
7) undertake studies on transport management system aiming at improving and fundamentally addressing road traffic safety issues, and implement same;
8) ensure that investigation of aircraft accidents are carried out in accordance with acceptable standards;
9) regulate transit services related to import and export of goods; and ensure that the national logistic system is efficient and competitive;

፲. የኢትዮጵያና ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅትን የሥራ እንቅስቃሴዎች በሁለቱ አገሮች መካከል በተደረገው ስምምነት መሠረት ይከታተላል፤

፲፩. ለአገሪቱ ጠቀሜታ ያላቸውን አማራጭ የወደብ አገልግሎቶች እያጠና ለመንግስት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ከወደብ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ከሌሎች ሀገራት ጋር የስምምነት ሰነዶችን ይፈራረማል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

፲፪.የአገሪቷን የትራንስፖርት መረጃዎች ያደራጃል፤ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል።

## ፳፪. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

፩. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የከተማ ልማትንና ኮንስትራክሽንን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ፣ የልማት ፓኬጆችን እና ፕሮግራሞችን ይቀርጻል ፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

ለ) አከታተምን በሚመለከት ጥናት ያካሂዳል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀትና አገራዊ ስፓሻል ፕላን እንዲሰራ በማድረግ የተቀናጀ የአከታተም ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ሐ) ከተሞች ከአገር አቀፍና ከክልል አቀፍ የልማት ዕቅዶችና ከተቀናጀ የከተሞች ፕላን ጋር ተጣጥመው የሚመሩበትን አቅጣጫ ይነድፋል፤

መ) ከክልሎች ጋር በመተባበር የከተሞች ልማት ከገጠር ልማት ጋር በተቀናጀ መንገድ የሚከናወንበትን ሁኔታ በሚመለከት ጥናቶችን ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፤ ከተሞች የአካባቢያቸው የልማት ማዕከል እንዲሆኑ ሁለገብና የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፤

ሠ) የተመጣጠነ የከተሞች ዕድገትና የህዝብ አሰፋፈር እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶችን ይነድፋል፤ ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል መንግሥታት አካላት ጋር በመቀናጀት ይተገብራል፤

ረ) የከተሞችን መሬት በቁጠባ መጠቀም የሚያስችል ዘመናዊ የአሰራር ስልት ይነድፋል ፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

10) follow up the operations of the Ethio-Djibouti Railways in accordance with the agreement concluded between the two countries;

11) initiate and submit to the government studies on alternative port services and oversee their implementation when approved; conclude port service agreements with other countries and follow up their implementation;

12) organize transport related data of the country, and disseminate same to concerned bodies;

## 22. The Ministry of Urban Development and Construction

1. The Ministry of Urban Development and Construction shall have the powers and duties to:

a) design and upon approval implement policies, strategies, development packages and programs relating to urban development and construction;

b) undertake studies relating to urbanization, in coordination with other relevant bodies establish system for integrated urban development and preparation of national spatial plan; follow up implementation of same;

c) outline directions that ensure compliance of urban centers with regional and national development schemes and integrated urbanization plans;

d) undertake studies for the integration of urban and rural development activities in collaboration with regional states; follow-up implementation of same; provide to urban centers all-round and coordinated support so as to make them development hubs of their surroundings;

e) design strategies that ensure balanced development and population settlement in urban centers; implement same in collaboration with the pertinent federal and regional government bodies;

f) put in place new procedures for economic use of urban land; follow up implementation of same;

ሰ) የከተሞችን ፈርጅ እና ሚና መወሰኛ መመዘኛ ያወጣል፤ የከተሞችን ፅዳት፣ ውበትና አረንጓዴ ልማት ስታንዳርድ ያወጣል፣ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

ሸ) ከተሞች የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ እና መልካም አስተዳደር እንዲያሰፍኑ ለክልሎች የአቅም ግንባታ እገዛ ያደርጋል፤ የመሠረተ ልማት አቅርቦትና አገልግሎት አሰጣጥ የተቀናጀ እንዲሆን ያደርጋል፤

ቀ) የከተማ ልማት ሥራ ከድህነት ቅነሳ ጋር የተቀናጀ እንዲሆን ጥናቶችን ያካሂዳል፤ ለተግባራዊነታቸውም ድጋፍ ይሰጣል፤ የከተማ የምግብ ዋስትና እና የሥራ ዕድል ፈጠራ እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤

በ) የአዲስ አበባና የድሬዳዋ የከተማ አስተዳደሮችን የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሥራ እንቅስቃሴዎች ይከታተላል፤

ተ) የነፃ ገበያ ሥርዓት ለማረጋገጥ የሚያስችል፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሚያሰፍን የካዳስተር እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ግብይት ሥርዓት እንዲገነባ ያደርጋል፤ በከተሞች ፍላጎትን መሠረት ያደረገ የለማ መሬት አቅርቦት ለማረጋገጥ ድጋፍ ይሠጣል፤

ቸ) የከተሞች ልማት ፋይናንስ ማጠናከሪያ ሥርዓት ያጠናል፣ በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ ያደርጋል፣ ፈንድ ያሰባስባል፣ ለአፈጻጸሙም ተቋማዊ አቅም እንዲፈጠር ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

ኀ) ለዜጎች የመኖሪያ ቤቶች አቅርቦት ለማሟላት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፤ በሚመለከታ ቸው አካላት ሲፀድቁም ተግባራዊነታቸውን ይደግፋል፤

g) set standards relating to categorization and role definition of urban centers; establish criteria for urban sanitation, beautification and greenery development; support and follow up implementation of same;

h) provide capacity building support to regions to improve service delivery and ensure good governance in urban centers; facilitate the integration of infrastructure and services provision;

i) undertake studies for integration of urban development with poverty reduction; support the implementation thereof; and ensure food security and job creation in the urban settings;

j) follow up the activities of Addis Ababa and Dire Dawa city administrations in relation to urban development and construction;

k) build cadaster and immovable property market systems that ensure transparency and accountability and enhance free market economy; provide support to ensure supply of developed urban land in accordance with demands in urban centers;

l) undertake study to establish urban development finance improvement system; cause its approval by the concerned organ; collect rising fund; provide support and follow-up to ensure institutional capacity building for implementation;

m) without prejudice to powers given by law to any other government organ, ensure the proper administration of houses owned by the Federal Government;

n) undertake studies on the provision of residential housing to citizens; and support implementation of same once approved by the concerned organs;

ነ) የኮንስትራክሽን ዘርፉን በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል የረጅም ጊዜ ስትራቴጂ ይነድፋል፣ ይተገብራል፤ ለዘርፉ ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ ጥናቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር ይተገብራል፤

ኘ) በዓለም አቀፍ ደረጃ የተወዳዳሪነት ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመገንባት የሚያስችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፤ በዲዛይን፣ በጨረታና፣ በኮንትራት ይዘት ላይ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

አ) በማንኛውም ዘርፍ የሚደረጉ የኮንስትራክሽን ሥራዎች ላይ ተገቢውን ቁጥጥር ያደርጋል፤ የኮንስትራክሽን ሥራዎችን ደረጃ ያወጣል፣ መከበራቸውን ይከታተላል፤

ከ) በፌደራል መንግሥት በጀት ለሚሠሩ ሕንፃዎች ዲዛይኖችና የግንባታ ውሎች እንዲዘጋጁ በማድረግና የግንባታ ሥራዎችን በመቆጣጠር ረገድ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

ኸ) የሕንፃ ኮድና ስታንዳርዶች በከተሞች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ተገቢው አደረጃጀት፣ አሠራርና የሰው ሃይል አቅም እንዲፈጠር ድጋፍ ያደርጋል፤

ወ) አገር በቀል የኮንስትራክሽን ድርጅቶችን ብቃትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ስትራቴጂ ይቀይሳል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ዐ) በኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚሰማሩ መሐንዲሶችና አርክቴክቶችን ይመዘግባል፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤የሥራ ተቋራጮችንና የአማካሪዎችን ደረጃ ይወስናል፤ ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥመሥራት ለሚችሉ የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

፪. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎችና ድንጋጌዎች ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር እና ለኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

o) design long term strategic plans that enhance proper management of the construction sector; implement same; execute studies on the development of the sector in coordination with pertinent bodies;

p) create conducive environment for the development of internationally competitive construction industry; establish transparent and accountable system for the management of design, bidding and contract contents; and follow up enforcement of same;

q) regulate construction works in all sectors; determine construction work standards; and follow up compliance with standards;

r) extend support in the preparation of designs, construction contracts and supervision of construction works involving buildings financed by federal budget;

s) support the development of appropriate organizational set-up, systems and human resource required for implementation of building codes and standards in cities;

t) design strategy to enhance the capacity and sustainability of local construction enterprises; follow up implementation of same;

u) register engineers and architects engaged in the construction sector; issue certificates of professional competence; determine the grades of contractors and consultants; issue certificates of competence to contractors and consultants operating in more than one regional states;

v) undertake research to improve the types and qualities of local construction materials;

2. The powers and duties given by provisions of other laws currently in force to the Ministry of Urban Development and Housing and the Ministry of Construction are hereby vested in the Ministry of Urban Development and Construction.

## ፳፫. የውሃ፣ መስኖና ኤነርጂ ሚኒስቴር

፩. የውሃ፣ መስኖና ኤነርጂ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

ሀ) የውሃ ሀብትና የመስኖ ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ ለዘርፉ ዕድገት የሚያስፈልጉ የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፍ ይቀርጻል፣ ሲፀድቅም አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

ለ) የተፋሰስ ጥናት በማካሄድ የአገሪቱን የከርሰ ምድርና ገጸ ምድር የውሃ ሀብት በመጠንና በጥራት ይለያል፣ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ሐ) ፍትሃዊ የውሃ አጠቃቀምን ለማስፈን የሚያግዝ ዘላቂ እና የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሥርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል፤

መ) በፌደራል መንግሥት በጀት የተገነቡ ግድቦችንና የውሃ ውቅሮችን ያስተዳድራል፤

ሠ) የአገሪቱ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እንዲያድግና ስርጭቱም እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ የኤሌክትሪክ ኃይል እጥረትን ለማስወገድ ከውሃ ኃይል፣ ከንፋስ ኃይል እና ከሌሎች አማራጭ የታዳሽ ኃይል ምንጮች ኤሌክትሪክ የማመንጨት ሥራን ይደግፋል፣ ይመራል፤

ረ) ከአንድ በላይ የሆኑ ክልሎችን አቋርጦ የሚፈስ ወይም የሚያዋስን ውሃ በልዩ ልዩ የአገልግሎት ዓይነቶችና በክልሎች መካከል ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ይወስናል፤

ሰ) አገራዊ ወሰን ተሻጋሪ የውሃ አካላት አጠቃቀም ላይ ጥናት ያካሂዳል፣ ለለም አቀፍ ውሎችን ይደራደራል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

ሸ) ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚውል ውሃ ሊኖረው የሚገባውን የጥራት ደረጃ ይወስናል፤ የውሃ ብክለትን እንዳይኖር ክትትል ያደርጋል፤

ቀ) የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትና የሳኒቴሽን መሠረተ ልማት ሽፋን እንዲያድግ እገዛ የሚያደርግ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

በ) የመካከለኛና የከፍተኛ መስኖ ልማት ሥራዎችን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የጥናት፣ የዲዛይንና የግንባታ ሥራዎች እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

## 23. The Ministry of Water, Irrigation and Energy

1. The Ministry of Water, Irrigation and Energy shall have the powers and duties to:

a) design policies and legal frameworks for the development of water resources and irrigation; upon approval follow up the implementation thereof;

b) undertake basin studies and verify the country's ground and surface water resource potentials in volumetric and quality terms, and facilitate utilization of same;

c) establish sustainable and integrated administration system facilitating the equitable utilization of water resources;

d) administer dams and water infrastructure financed by federal budget;

e) ensure the development of electric power provisions and enhance distribution of same; generate, stock and distribute energy produced from water, wind and other alternative renewable energy sources and alleviate shortfalls in electric power provision;

f) determine conditions for optimum and equitable allocation and utilization of water bodies that traverse across or lie between more than one regional states among various uses and regional states;

g) undertake studies pertaining to utilization of national and transboundary water resources; negotiate international treaties; follow up implementation of same;

h) determine quality standards of water used for various purposes; undertake monitoring works to avert water pollution;

i) establish system that facilitates the expansion of potable water supplies and coverage of sanitation infrastructure; follow up implementation of same;

j) cause the carrying out of study, design and construction works to promote the expansion of medium and large irrigation development schemes;

ተ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ረ) እና (ሰ) በተጠቀሱት የውሃ አካሎች ላይ የውሃ ሥራዎች ለመሥራትና በጥቅም ላይ ለማዋል ፈቃድ ይሰጣል፣ይቆጣጠራል፤

ቸ) የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት እንዲስፋፋ ድጋፍ ያደርጋል፣ ከዘርፉ የሚገኘውን መረጃዎች የመጠቀም አቅምን ያሳድጋል፤

ኀ) የውሃ ሀብት መረጃና ኢንፎርሜሽን ሥርዓትን ይዘረጋል።

፪. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች ለውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለውሃ፣ መስኖና ኤነርጂ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## ፳፬. የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር

፩. የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

ሀ) የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማትን የሚመለከቱ የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፍ ይቀርጻል፣ ሲፀድቅም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ለ) የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ የምርምርና የማሠልጠኛ ተቋሞችን እንዳስፈላጊነቱ ያደራጃል፤

ሐ) በማዕድን፣ በነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማት መስክ በየደረጃው የሚፈለገውን የሰው ሀብት ለማልማት ከትምህርት ተቋማትና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

መ) የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ የስነ ምድር ካርታ ሽፋን ጥራትን ያሳድጋል፣ የመረጃዎችን ተደራሽነት ያረጋግጣል፤

ሠ) ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በባህላዊና በአነስተኛ ደረጃ የሚመረቱ የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናት ግብይት ውጤታማና ቀልጣፋ እንዲሆን ሥርዓት ይዘረጋል፤ በመስኩ ለሚሰማሩ አልሚዎች አበረታች ፖሊሲ ይቀርጻል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ያስፈጽማል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

ረ) በባህላዊ መንገድ ማዕድን ማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦችን ያደራጃል፣ አቅማቸውን ይገነባል፤

ሰ) ኢንቨስትመንትን በማበረታታት የማዕድን፣ ነዳጅ፣ የተፈጥሮ ጋዝ ፍለጋና ልማት እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ ተጨማሪ ዕሴት ያላቸው ምርቶችን ያበረታታል፤

k) issue permits and regulate the construction and operation of water works relating to water bodies referred to in paragraphs (f) and (g) of this sub-article;

l) provide support to promote expansion meteorological services; enhance capacity to utilize data obtained from the sector;

m) put in place water resources data and information system;

2. The powers and duties given to the Ministry of Water, Irrigation and Electricity by provisions of other laws currently in force are hereby vested in the Ministry of Water, Irrigation and Energy.

## 24. The Ministry of Mines and Petroleum

1. The Ministry of Mines and Petroleum shall have the powers and duties to:

a) design policies and legal frameworks pertaining to the development of minerals, petroleum and natural gas; when approved follow up implementation thereof;

b) organize research and training institutions that accelerate the development of minerals, petroleum and natural gases, as may be necessary;

c) work in partnership with educational institutions and other pertinent bodies to produce variously trained manpower required in the development of minerals, petroleum and natural gases;

d) ensure the quality and accessibility of geophysical map and data on minerals, petroleum and natural gas;

e) put in place, in cooperation with concerned bodies, system that enhances the efficiency and effectiveness of marketing in precious and ornamental minerals produced in small scales; design and implement policy that encourages small-scale mining operations once approved by the concerned body;

f) organize and build the capacity of individuals engaged in traditional mining operation;

g) promote investment by creating favorable conditions for the expansion of exploration and mining operations; encourage value added products;

ሸ) የነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ምርት ፍለጋን በበላይነት ይመራል፣ ምርቱን ወደ ገበያ ለማሸጋገር የሚያስችል ዘመናዊ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን ይፈጥራል፤

ቀ) በማዕድን፣በነዳጅና በተፈጥሮ ጋዝ ፍለጋና ልማት ለሚሠማሩ የግል ባለሃብቶች ፈቃድ ይሰጣል፣ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤ በገቡት ውል መሠረትም ሥራቸውን ማካሄዳቸውንና የክፍያ ግዴታቸውን መፈጸማቸውን ይቆጣጠራል፤

በ) የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች ለነዋሪዎች የሥራ ዕድል የሚፈጠርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ከመሠረተ ልማቱ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

ተ) የተፈጥሮ ጋዝና የነዳጅ ምርቶችን የጥራት ደረጃ ያረጋግጣል፣ የማከማቻና ማከፋፈያ ተቋሞችን ደረጃ ይወስናል፣ ተፈጻሚነቱን ይከታተላል፤

ቸ) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የነዳጅና መጠባበቂያ ክምችትን መጠን ይወስናል፣ ክምችቱ እንዲኖር መደረጉን ያረጋግጣል፤

ኀ) ከማዕድን፣ ከነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶችን ይደራደራል፣ ይፈርማል፤

ነ) የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝን የተመለከቱ መረጃዎች በአግባቡ እንዲሰበሰቡ፣ እንዲጠበቁና ለተጠቃሚዎች እንዲቀርቡ ያደርጋል።

፪. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎችና ድንጋጌዎች ለማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

፳፭. **<u>የትምህርት ሚኒስቴር</u>**

የትምህርት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩. የትምህርትና ሥልጠና ስታንዳርድ ያወጣል፤ በሥራ ላይ መዋሉንም ያረጋግጣል፤

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) አገራዊ የብቃት ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤

h) lead and oversee the exploration of petroleum and natural gas; organize modern system and institutional set up for the supply of products to markets;

i) issue licenses to private investors engaged in mining and exploration of petroleum and natural gas; provide appropriate support; and ensure that such investors operate in accordance with the agreements concluded and meet their financial obligations;

j) create conditions for the employment of local communities in areas where mining operations and explorations of petroleum and natural gas are pursued; put in place conducive environment to ensure that local communities benefit from such infrastructure developments;

k) ensure quality standards of petroleum and natural gas products; set standards for petroleum storage and distribution facilities; follow up enforcement of same;

l) determine, in cooperation with the appropriate organs, the volume of petroleum reserve and ensure that such reserve is maintained;

m) negotiate and sign international treaties pertaining to mining, petroleum and natural gas;

n) ensure that information relating to mining, petroleum and natural gas is collected, maintained and availed for utilization by users;

2. The powers and duties given to the Ministry of Mines, Petroleum and Natural Gas by provisions of other laws currently in force are hereby vested in the Ministry of Mines and Petroleum.

25. **<u>The Ministry of Education</u>**

The Ministry of Education shall have the powers and duties to:

1. set education and training standards; ensure implementation of same;

2. without prejudice to the generality of sub-article (1) of this Article:

a) formulate a national qualification framework;

ለ) አጠቃላይ የሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤

ሐ) የመምህራን የትምህርት ብቃት መለኪያ ያወጣል፤

መ) የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ሊያሟሉ የሚገባቸውን ደረጃ ያወጣል፤

፫. የከፍተኛ ትምህርትና የቴክኒክና ሙያ ተቋማትን ሳይጨምር በየደረጃው ባሉ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ጥራትና አግባብነት ያለው ትምህርትና ሥልጠና መሰጠቱን ያረጋግጣል፤

፬. የአገሪቱን የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲና ሥርዓተ-ትምህርት መሠረት ያደረጉ አገር አቀፍ ፈተናዎች ዝግጅት፣ ሪከርድ መያዝና የምስክር ወረቀት የመስጠት ሂደቶችን በበላይነት ይመራል፤

፭. ትምህርትና ሥልጠናን በተመለከተ አገራዊ የአህዝቦት ተግባራትን ያከናውናል።

## ፳፮. የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር

፩. የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የከፍተኛ ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣ በበላይነት ይመራል፤

ለ) የከፍተኛ ትምህርት ከአገሪቱ አጠቃላይ የልማት ፖሊሲና ከዘርፎች ዕድገት ጋር አብሮ ለማስኬድ የሚያስችል ስትራቴጂ ይነድፋል፣ በሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ) የአገሪቱን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂ ይቀርጻል፤ በሚመለከታቸው አካላት ሲጸድቅም በሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል።

መ) የከፍተኛ ትምህርትና ቴክኒክና ሙያ ተቋማት በመሠረታዊ የሳይንስ ጥናትና ምርምር የጎለበቱ እንዲሆኑ የሚያስችል ስልት ይነድፋል፣ ይተገብራል፤ የሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር ውጤቶች በሥራ ላይ የሚውሉበትን መንገድ ያመቻቻል፤

ሠ) በከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪው ዘርፍ መካከል ለምርምርና ቴክኖሎጂ ልማት እንቅስቃሴ የሚያግዝ ምቹ የርስበርስ ትስስርና ቅንጅታዊ አሠራር እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

b) formulate a general framework of education curricula;

c) set minimum educational qualification requirements for school teachers;

d) set minimum standards for education and training institutions;

3. ensure that quality and relevant education and training are offered at all levels of the education and training centers excluding higher education and technic and vocational institutes;

4. prepare and administer national examinations based on the country's education and training policy and curricula; lead the functions of maintaining records and issuing certificates;

5. publicize national performance in education and training.

## 26. The Ministry of Science and Higher Education

1. The Ministry of Science and Higher Education shall have the powers and duties to:

a) ensure the expansion of higher education; oversee the sector;

b) undertake and implement strategies that seek to synchronize higher education with the country's overall developmental policies and sectoral specific developments;

c) design strategy and upon approval follow up the implementation of the country's technical and vocational education and training;

d) design strategies to augment higher education and technical and vocational education institutions' capacity in basic scientific studies and research; implement same; device opportunities for operationalization of scientific studies and research results;

e) create conducive environment for technology development and operations by facilitating linkages and coordinated working procedures between higher education institutions and the industry sector;

ረ) የከፍተኛ ትምህርት የሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ ያዘጋጃል፣

ሰ) የከፍተኛ ትምህርትና ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ሊያሟሉ የሚገባቸውን ደረጃ ያወጣል፣ በተቋማቱ ጥራትና አግባብነት ያለው ትምህርትና ሥልጠና መሠጠቱን ይከታተላል፣

ሰ) የመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን አፈጻጸም ይከታተላል፣

ሸ) የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቅበላና ምደባ አፈጻጸም ፍትሃዊ መሆኑን ያረጋግጣል፣

፪. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎችና ድንጋጌዎች ከፍተኛ ትምህርት እና ቴክኒክና ሙያን በሚመለከት ለትምህርት ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት፣ ሳይንስን በሚመለከት ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## ፳፯. የጤና ሚኒስቴር

የጤና ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩. የጤናውን ዘርፍ ልማት አገራዊ ፕሮግራም ይነድፋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

፪. የጤና ሥርዓቱን ካርታ ያዘጋጃል፣ የጤና መሠረተ ልማቶች እንዲስፋፉ ድጋፍ ያደርጋል፣

፫. የጤና አገልግሎት ሽፋን እንዲያድግ እገዛ ያደርጋል፣ የጤና ፕሮግራሞችን አፈጻጸም ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣

፬. የአገሪቱን የጤና ችግር ለመፍታትና የጤና አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የሚረዱ ምርምሮች እንዲካሄዱ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣

፭. አገራዊ የአመጋገብ ሥርዓት ስትራቴጂ አፈጻጸምን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣

፮. ወረርሽኝና ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣

፯. የኅብረተሰቡን ጤና ሊጎዱ የሚችሉ ሁኔታዎችን የመከላከል እርምጃ ይወስዳል፣ ድንገተኛ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ የሌሎች አካላት ሥራዎችን በማስተባበር ለችግሩ አፋጣኝና ውጤታማ መፍትሄ ይሰጣል፣

f) prepare higher education curricula framework;

g) set standards required for higher education and technical and vocational education institutions; follow up the delivery of appropriate education and training in these institutions

h) follow up the performance of state-owned higher education institutions;

i) ensure that the implementation of student admissions and placements in higher education institutions are equitable;

2. The powers and duties given by provisions of other laws currently in force to the Ministry of Education in relation to matters pertaining to higher education and technical and vocational education; and to Ministry of Science and Technology pertaining to science are hereby vested in the Ministry of Science and Higher Education.

## 27. Ministry of Health

The Ministry of Health shall have the powers and duties to:

1. formulate the country's health sector development program; follow up and evaluate the implementation of same;
2. prepare the country's health services coverage map; provide support for the expansion of health infrastructure;
3. support the expansion of health services coverage; follow up and coordinate the implementation of health programs;
4. provide appropriate support to promote research activities intended to provide solutions for the country's health problems and for improving health service delivery;
5. follow up and coordinate the implementation of national nutrition strategies;
6. devise and follow up the implementation of strategies for the prevention of epidemic and communicable diseases;
7. take preventive measures against events that threaten the public health; in the events of an emergency situation coordinate measures of other stakeholders to expeditiously and effectively tackle the problem;

፰. አግባብነት ያላቸውን የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም የጤና አጠባበቅ ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

፱. በአገሪቱ ውስጥ የአስፈላጊ መድሃኒቶችና የሕክምና መሣሪያዎች በቂ አቅርቦት መኖሩንና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

፲. የፌደራል ሆስፒታሎችን አስተዳደር በበላይነት ይቆጣጠራል፤ የፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች ሆስፒታሎችን አቅም በማጎልበት ረገድ ተባብሮ ይሠራል፤

፲፩. በአገሪቱ ውስጥ የሚሰጠው የጤና ባለሙያዎች ሥልጠና ጥራትና አግባብነት ባለው ሁኔታ እንዲካሄድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይተባበራል፤

፲፪. የምግብ፣የመድኃኒትና ጤና እንክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራዎች በአግባቡ መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፤

፲፫. አገራዊ የጤና መድህን ሥርዓቱን ይመራል፤ አፈፃፀሙንም ይቆጣጠራል፤

፲፬. አገራዊ የጤና መረጃ ሥርዓቱን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል።

**፳፰. <u>የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር</u>**

፩. የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

ሀ) ሴቶችና ወጣቶች በአገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችሏቸው ዕድሎች የተመቻቹላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ይነድፋል፣ ያስፈጽማል፤

ለ) የሴቶችና የሕፃናት መብቶችን በተመለከተ ግንዛቤ የመፍጠር እንቅስቃሴን ይመራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

ሐ) ሴቶች በተለያዩ የመንግሥት አካላት በውሳኔ ሰጪ የሥራ ቦታዎች ለመመደብ በቂ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤

መ) በአገር አቀፍ ደረጃ የሴቶች ልዩ ድጋፍ መብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ስልት ይቀይሳል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

ሠ) በሴቶች ላይ የሚቃጡ መድሎዎችን በጥናት በመለየት መድሎዎቹ የሚወገዱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

8. expand health education through various appropriate means;
9. ensure adequate supply and proper utilization of essential drugs and medical equipment in the country;
10. supervise the administration of federal hospitals; collaborate on the capacity building activities of the federal university hospitals;
11. collaborate with the appropriate bodies in providing quality and relevant health professional trainings within the country;
12. ensure the proper execution of food, medicine and health care administration and regulatory functions;
13. lead the national social health insurance system and oversee its implementation;
14. direct, coordinate and follow up implementation of the country's health information system.

**28. <u>Ministry of Women, Children and Youth</u>**

1. The Ministry of Women, Children and Youth shall have the powers and duties to:

a) design strategiec plan to ensure that opportunities are created for women and youth to actively participate in political, economic and social affairs of the country and implement same;

b) lead and support activities of awareness creation and movement on the rights of women and children;

c) ensure that due attention is given to assign women for decision-making positions in various Government organs;

d) devise means for the proper application of women's right to affirmative action guaranteed at the national level and follow up the implementation of same;

e) undertake studies to identify discriminatory practices affecting women, facilitate the creation of conditions for the elimination of such practices, and follow up their implementation;

ረ) በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጾታዊ ጥቃቶችን በአግባቡ ለመከላከል እንዲሁም ጥቃቶች ሲፈጸሙ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ስትራቴጂ ይነድፋል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በሥራ ላይ ያውላል፤

f) design strategies to effectively prevent and take measures against gender-based violence against women; implement same in collaboration with relevant organs;

ሰ) ጥቃት የተፈጸመባቸው ሴቶች የተሟላ የጤና፣ የስነ-ልቦና፣ የሕግና የተሃድሶ አገልግሎት የሚያገኙባቸው ማዕከላት እንዲቋቋሙ ድጋፍ ይሰጣል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፤

g) facilitate the setting up centers for provision of holistic health, psychological, legal and rehabilitation services for women who were victims of violence; and follow up the implementation of same;

ሸ) ሴቶችና ወጣቶች እንደፍላጎቶቻቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸው እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንዲችሉ ያበረታታል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

h) encourage and support women and youth to be organized, based on their interests and needs, with a view to defending their rights and solving their problems;

ቀ) ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር ሴቶችና ወጣቶች በተለያዩ ዘርፎች የሚሰማሩባቸውን የሥራ ዕድሎች በጥናት ይለያል፤ በኅብረት ሥራ ማኅበራት ተደራጅተው ተጠቃሚ የሚሆኑባቸው ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ይቀርጻል፤ አተገባበሩንም ይከታተላል፤

i) in collaboration with the relevant organs, conduct studies to identify areas of job opportunities for women and youth; design programs and projects so women and youth can benefit from these opportunities by organizing themselves in to cooperative associations;

በ) ለሴቶችና ወጣቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠርና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያግዙ የልማት ፈንዶች የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

j) facilitate the setting up of development funds to create job opportunities for and ensure economic benefits to women and youth;

ተ) በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙ ሴቶችና ወጣቶችን ኑሮ ለማሻሻል፣ የቁጠባ ባህላቸውን ለማዳበር፣ በአማራጭ ኤነርጂና በሌሎች የተለያዩ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፣

k) work in collaboration with relevant organs to support women and youth living in poverty to improve their livelihoods through improving saving culture, using alternative energy sources and use other appropriate technology;

ቸ) በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ጥቃቶችን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይነድፋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

l) design techniques to prevent harmful practices that cause harm to women and children; implement same upon approval;

ኀ) የሕፃናት መብትና ደኅንነት እንዲጠበቅ የሚመለከታቸውን አካላት ሁሉ ያስተባብራል፤

m) coordinate actions of all stakeholders to protect the rights and well-being of children;

ነ) የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር የሕፃናት መልካም አስተዳደግና ሰብዕና ግንባታ፣ ድጋፍ፣ እንክብካቤ እና ተሀድሶ ላይ ለወላጆችና አሳዳጊዎች ተገቢውን ግንዛቤና ሥልጠና በመሥጠት ላይ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል፤

n) coordinate actions of all stakeholders to exert a concerted effort towards providing the proper awareness-creation and training on good parenting, character building, support, care and rehabilitation for parents and caretakers;

አ) በተለያዩ ምክንያቶች ለችግር የተጋለጡና ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት ጉዲፈቻን ጨምሮ በአገር ውስጥ ባሉ አማራጭ ድጋፍና እንክብካቤ ዘዴዎች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤ በዓለም አቀፍ ጉዲፈቻ ከአገር የወጡ ኢትዮጵያዊ ሕፃናት በእንክብካቤ እንደተያዙ ለማረጋገጥ ጉዳያቸውን ይከታተላል፤

ከ) ሕፃናትን ከአገሪቱ ልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የልማት ተቋማት ማኅበራዊ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ስልት ይቀይሳል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

ኸ) ቤተሰብ እንደኅብረተሰብ ዋና መሠረት የተሰጠውን ሕገ-መንግሥታዊ ጥበቃ በተግባር ለማዋል የሚያስፈልጉ ስልቶችን ከሚመለከታቸው ክልላዊ መንግሥት አካላትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ይነድፋል፤ ተግባራዊነቱን ይከተላል፤

ወ) በፌደራል መንግሥት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ እንዲያካትቱ ስልት ይነድፋል፣ ይገመግማል፣ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

ዐ) ሴቶችና ሕፃናትን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ውሎችን በሕግ መሠረት ይዋዋላል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤ ለሚመለከታቸው አካላትም ሪፖርት ያቀርባል፤

ዘ) የሴቶች፣ የሕፃናትና የወጣቶችን ሁኔታ የሚያመለክቱ ዝርዝር መረጃዎች ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ በሚመለከታቸው ሁሉ እንዲታወቁ ያደርጋል።

፪. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎችና ድንጋጌዎች ለሴቶችና ሕፃናት ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት ፣ወጣቶችን በሚመለከት ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

**፳፱. <u>የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር</u>**

የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩. የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጎች፣ የሠራተኞች አስተዳደር ሕጎች በተክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

o) design strategies to ensure local options of care and support, including adoption, for orphaned children and children exposed to risk due to various reasons; implement same upon approval; follow up care taking of children adopted abroad;

p) design strategies to ensure that government and private actors carry out their obligations to guarantee that children are beneficiaries of the development of the country; follow up implementation of same;

q) in collaboration with the relevant regional government organs and other relevant bodies, design techniques necessary to implement the constitutional protection given to the family as the fundamental unit of society; follow up implementation of same;

r) design strategies to follow up and regulate that the preparation of policies, legislations, development programs and projects by Federal Government organs give due considerations to the issues of women, children and the youth;

s) conclude international treaties relating to women and children in accordance with law and, follow up the implementation of same and submit reports to the concerned bodies;

t) collect, compile and disseminate to relevant stakeholders information on the objective realities of women, children and the youth.

2/ The powers and duties given to the Ministry of Women and Children Affairs by the provisions of other laws, currently in force, with respect to women and children and to the Ministry of Youth and Sports with respect to the youth are hereby vested in the Ministry of Women, Children and Youth.

**29. <u>Ministry of Labor and Social Affairs</u>**

The Ministry of Labor and Social Affairs shall have the powers and duties to:

1. ensure and follow up the proper enforcement of labor laws and administrative rules;

፪. ተቀማጭነታቸው ከአንድ ክልል በላይ የሆኑ ድርጅቶችን የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

፫. በሥራ ላይ የሚከሠቱ አደጋዎችና በሥራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ የሙያ ጤንነትና ደኅንነት ደረጃዎች ያወጣል፣ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤

፬. የኢንዱስትሪ ሠላም ለማስጠበቅ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል ፣ ተግባራዊነቱንም ያረጋግጣል፤

፭. አሠሪዎችና ሠራተኞች በማኅበር የመደራጀትና የሕብረት ድርድር የማድረግ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ ያበረታታል፣ ይደግፋል፤

፮. በአሠሪዎችና በሠራተኞች መካከል የሁለትዮሽ፣ እንዲሁም የመንግሥት ወገንን ጨምሮ የሶስትዮሽ የውይይት መድረኮች እንዲደረጉ ድጋፍ ያደርጋል፤

፯. በአገር አቀፍ ደረጃ የሚደራጁትን የሠራተኛና የአሠሪ ማኅበራት ይመዘግባል፤

፰. በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች ውስጥ የሚገኙ የፌደራል መንግሥት የልማት ድርጅቶችን የሚመለከቱ የሠራተኛ ማኅበራትንና የሕብረት ስምምነቶችን ይመዘግባል፤ በእነዚሁ ድርጅቶች ውስጥ የሥራ ሁኔታ ቁጥጥር አገልግሎት ተግባሮችን ያከናውናል፤ በአሠሪዎችና በሠራተኞች መካከል የሚነሱ የሥራ ክርክሮችን በስምምነት ለመጨረስ የማስማማት አገልግሎት ይሰጣል፤

፱. የሥራ ክርክሮችን ክስተት ለመቀነስ የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፤ ሲከሰቱም መፍትሄ የሚያገኙበት የተቀላጠፈ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈጽማል፤

፲. የአሠሪና ሠራተኛ ብሔራዊ የመረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አገራዊ የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፩. የማኅበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን በማጠናከር የዜጎች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደኅንነት እና ዋስትና የሚሻሻሉባቸውና የሚጠበቁባቸው ዘዴዎችን በሚመለከት በተለይም፡-

ሀ) የአካል ጉዳተኞች እኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ፣

ለ) አረጋዊያን እንክብካቤና ድጋፍ እንዲያገኙና ተሳትፏቸው እንዲጎለብት፣

2. follow up and support the labor relation of enterprises situated in more than one Regional State;

3. establish a system to prevent occupational accidents and occupational diseases; issue occupational health and safety standards and supervise their implementation;

4. set up a system to ensure industrial peace and ensure its proper implementation;

5. encourage and support employers and workers to form organizations and thereby exercise their rights of collective bargaining;

6. encourage the practice of bipartite forums between workers and employers and tripartite forums involving the Government;

7. register employers' association and trade unions established at national level;

8. register trade unions and collective agreements relating to Federal Public Enterprises situated inAddis Ababa and Dire Dawa cities; carry out labor inspection services in such enterprises; provide conciliation services to amicably settle labor disputes arising between employers and employees;

9. set a mechanism to minimize occurrence of labor disputes and establish efficient system for settlement of same;

10. establish national labor sector information system and realize its implementation; establish and put into operation a national labor market information system;

11. work in collaboration with the concerned bodies to strengthen the social protection system to improve and ensure the social and economic wellbeing of citizens and, in particular to:

a) enable persons with disabilities benefit from equal opportunities and full participation;

b) enable the elderly to get care and support and enhance their participation;

ሐ) የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመከላከልና በችግሩ ውስጥ የሚገኙ በተለይም አረጋውያንና የአካል ጉዳተኞች አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ፣

ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

፲፪. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በተመባበር መደበኛ ያልሆነውን የኢኮኖሚ ዘርፍ ወደ መደበኛ ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት በአሠሪና ሠራተኛ አስተዳደር ግንኙነት ዙሪያ ይዘረጋል፤

፲፫. ቀልጣፋና ፍትሐዊ የሥራ ስምሪት አገልግሎቶች ተደራሽነት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

፲፬. ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፤

፲፭. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የኢትዮጵያውያን የውጭ አገር የሥራ ስምሪትን ይቆጣጠራል።

## ፴. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩. በኢትዮጵያ የሚገኙ ልዩ ልዩ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶችና ዕሴቶች እንዲጠኑና እንዲጠበቁ ያደርጋል፤

፪. በባህል ዘርፍ የሕዝቡን ተሳትፎ ተቋማዊ መሠረት ለማስያዝ የባህል ተቋማት እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

፫. ማኅበራዊ እድገትን የሚያጓትቱ አመለካከቶችን፣ እምነቶችንና ልማዳዊ አሰራሮችን የመለወጥ ተግባሮች ያከናውናል፤

፬. የዕደ ጥበብ፣ ኪነ ጥበብና የሥነ-ጥበብ ሥራዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤ የአገሪቱ የፊልምና ተውኔት ጥበብ ሥራዎች የሚያድጉበትን አግባብ ያመቻቻል፤

፭. በዘርፉ ውጤታማ የፈጠራ ሥራዎችን ላበረከቱ ግለሰቦችና ተቋማት ሽልማትና ማበረታቻ የሚሰጥበት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፤

፮. በኢትዮጵያ የሚገኙ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች እንዲጠኑ፣ ስነ-ጽሑፎቻቸው እንዲዳብሩና እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

፯. የትርጉም አገልግሎትና የአስተርጓሚነት ሙያ ዕውቀት እንዲዳብርና እንዲስፋፋ የሚያደርጉ ተግባሮችን ያከናውናል፤ ደረጃውን የጠበቀ የሥራ ቋንቋ አጠቃቀም እና የትርጉም አገልግሎት እንዲኖር ይደግፋል፣ ክትትል ያደርጋል፤

c) prevent social and economic problems and provide the necessary services to segments of the society under difficult circumstances particularly the elderly and people with disabilities;

12. in cooperation with concerned bodies, establish a labor administration system around the labor relation that enables the proper transition of the informal economy to the formal economy;

13. enhance the accessibility of efficient and equitable employment services;

14. issue work permits to foreign nationals and, in cooperation with concerned bodies, supervise the compliance therewith;

15. in cooperation with concerned bodies, regulate the Ethiopians overseas employment;

## 30. Ministry of Culture and Tourism

The Ministry of Culture and Tourism shall have the powers and duties to:

1. cause the study and preservation of history, cultural heritages and values of the various peoples in Ethiopia;
2. expand cultural institutions to institutionalize public participation in the development of culture;
3. undertake activities to bring about changes in cultural attitudes, beliefs and practices hindering social progress;
4. promote creativity in handicraft, artistic works and fine art; create conducive environment for the development of the country's film industry and theatrical arts;
5. establish and enforce a working procedure for awarding and motivating those individuals and institutions with outstanding achievements in creative industry;
6. cause the study of the various languages in Ethiopia and the advancement and promotion of their literatures;
7. undertake activities related to advancement and promotion of translation services and translation as a professional knowledge; assist and follow up standard usage of working language and translation services;

፰. የቱሪዝም ዘርፍን ዕድገት ለመምራት የሚያስችል ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ይነድፋል፣ ይተገብራል፤

፱. ዓለም አቀፍና የአገር ውስጥ ቱሪዝም እንዲስፋፋ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

፲. የአገሪቱ የተፈጥሮ ቅርሶች እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ በፌደራል መንግስት እንዲተዳደሩ የተሰየሙ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር በአግባቡ እንዲመሩ ለሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ ያደርጋል፤

፲፩. በሰው ኃይል ሥልጠናና በሙያ ምክር አገልግሎት አማካኝነት የባህልና የቱሪዝም ሴክተርን የማስፈጸም አቅም ይገነባል፤

፲፪. የባህልና ቱሪዝም መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያሰራጫል።

## ፴፩. የገቢዎች ሚኒስቴር

፩. በሥራ ላይ ባሉ ሕጎች ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተሰጡት ሥልጣንና ተግባሮች በዚህ አዋጅ ለገቢዎች ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

፪. የጉምሩክ ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራቱ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

## ፴፪. ስለሌሎች አስፈጻሚ አካላት

፩. የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል ፤ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

ሀ) በአገር አቀፍ ደረጃ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሰው ሀብት ልማት በቀጣይነት የሚለማበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ስልት ይቀይሳል፤

ለ) የመንግሥት ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥ በቀጣይነት የሚሻሻልበትን ስልት ይቀይሳል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣ ይገመግማል፤ የመንግሥት ዘርፍ አቅም ግንባታ ሥራዎችን ያስተባብራል፤

ሐ) የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች ምልመላና መረጣ በብቃት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ያደርጋል፤

8. design and implement a strategy to enhance the growth of the tourism sector;

9. create conducive environment for expansion of international and domestic tourism;

10. facilitate the studying and preservation of the country's natural heritages and the development and utilization of them as tourist attractions; support the work of concerned organs to ensure the proper management of wildlife conservation areas designated to be administered by the Federal Government;

11. build the capacity of the culture and tourism Sector through the provision of human resource training and consultancy supports;

12. collect, compile and disseminate information on culture and tourism.

## 31. Ministry of Revenues

1. The powers and duties given to the Ethiopian Revenues and Customs Authority by the provisions of laws currently in force are hereby vested in the Ministry of Revenues.
2. The Customs Commission is hereby established. The powers and duties of the Commission shall be specified through Regulation to be issues by the Council of Ministers.

## 32. Other Federal Executive Organs

1. The Civil Service Commission is hereby established. The Commission shall have the powers and duties to:

a) adopt strategies for continuous human resource development and deployment activities of executive organs of the government;

b) adopt strategies for continuous improvement of service delivery in the public sector; coordinate public sector capacity building activities; monitor and evaluate the implementation of same;

c) ensure that the recruitment and selection of the federal civil servants is primarily based on merit;

መ) ብቃት ያለውና ውጤታማ አመራርና ሲቪል ሰርቪስ እንዲገነባ ስልት ይቀይሳል፣ የብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

d) adopt strategies for building competent and effective leadership and public service; establish systems to ensure competence and follow up the implementation of same;

ሠ) የሲቪል ሰርቪሱ በብቃትና በአፈጻጸም ላይ የተመሠረተ የክፍያና የማበረታቻ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፤ ውጤታማነቱን ይገመግማል፣ አስፈላጊውን የማሻሻያ እርምጃ ይወስዳል፣

e) establish competence and performance-based pay and reward system for the public service; evaluate its effectiveness and make necessary adjustments;

ረ) የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች አስተዳደር ሕጎች በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ የሠራተኞች ሥነ-ምግባር መከታተያ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ ያረጋግጣል፤

f) follow up and ensure the proper enforcement of Federal public servants' administration laws; establish a system to monitor ethics of Federal public servants', and follow up the implementation of same;

ሰ) የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችን የውስጥ አደረጃጀት አግባብነት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤ በአደረጃጀት ማሻሻያ ጥናት ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤ የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤቶችን የሥልጣንና ተግባራት ወሰን፣ አወቃቀርና አደረጃጀትን በተመለከተ ጥናት በማካሄድ ለመንግስት የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

g) review and decide on the appropriateness of the internal organizational structures of Federal Government offices; provide necessary support in conducting reform studies; conduct studies and make recommendations to the Government on mandate, accountability and structure of Federal Government institutions;

ሸ) በፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ፣ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፤

h) ensure that Federal Government offices establish and implement service delivery standards, complaint submission and handling procedures for customers;

ቀ) የሲቪል ሰርቪሱ የሰው ሃብት አመራር መረጃዎች ሥርዓት በወጥነት እንዲዳብርና እንዲተገበር ያደርጋል፤ ማዕከላዊ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፤

i) ensure the development and implementation of uniform information system on human resource management of the public service and serve as a central information clearing house;

በ) በሕግ መሠረት የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞችን ከጡረታ ዕድሜ ክልል በላይ በአገልግሎት ላይ ስለማቆየት በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

j) decide on requests for authorization of retention of public servants in service beyond retirement age as per the relevant laws;

ተ) በመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች በሚቀርብ ይግባኝ ላይ የፍሬ ነገር የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤

k) give final decisions on the issue of fact on appeals of public service employees on the basis of public service laws;

ቸ) በፌደራል ደረጃ የሚከናወኑ የካይዘን አመራር የለውጥ ሥራዎች በአግባቡ መከናወናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።

l) follow up and supervise the proper execution of Kaizen based reform activities conducted at the federal level.

፪. ቱሪዝም ኢትዮጵያ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

2. Tourism Ethiopia is hereby established; it shall have the powers and duties to:

ሀ) የተለያዩ የቱሪዝም ባለድርሻ አካላት የሚያከናውኗቸውን የቱሪዝም ማርኬቲንግ እንቅስቃሴዎች በማቀናጀትና በመምራት የአገሪቱን የቱሪዝም ሃብቶች፣ መስህቦችና መልካም ገፅታ በውጭ አገርና በአገር ውስጥ በስፋት ያስተዋውቃል፤

ለ) ሥልጣንና ተግባራቱን ለማስፈጸም እንዲያስችለው የቱሪዝም ፈንድ ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የአገሪቱ የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁ ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና እንዲደራጁ ስልት ነድፎ ይተገብራል ፤ መስህቦችና የአገልግሎቶች መረጃ ማዕከላትን በመግቢያ በሮችና በማዕከል ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ይመራል፤

መ) የአገሪቱ የቱሪስት መስህቦች በቅድመ ሁኔታነት የተቀመጡ መስፈርቶችን በማሟላት በዓለም አቀፍ ቅርስነት የሚመዘገቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

ሠ) የአገሪቱን የቱሪዝም መስህቦች፣ ምርትና አገልግሎቶች መለያ በመቅረጽና በየጊዜው በማሻሻል በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

ረ) የማርኬቲንግ ተግባራትን ለማከናወን የሚረዱ መረጃዎችንና የጥናት ዓይነቶችን ይለያል፣ ያሰባስባል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ያሰራጫል፤

ሰ) የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደረጃዎች ይወስናል፣ ተፈጻሚነቱን ይቆጣጠራል፤

ሸ) የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እንዲስፋፉ፣ የየአካባቢው ማኅበረሰብም ከቱሪዝም ጥቅሞች ተካፋይ እንዲሆን የሚደረግበትን አግባብ ያመቻቻል፤

ቀ) የቱሪዝም ልማትና ማርኬቲንግ የአገልግሎት ክፍተት በመለየት የሥልጠና ፍላጎቶች የሚሟሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

በ) ከቱሪዝም ተዋናዮች ጋር አጋርነትና ትብብር ይፈጥራል፤

ተ) የቱሪዝም ዘርፉን ዕድገት ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ ጥናቶችን ያከናውናል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅ ይተገብራል፤

ቸ) ነባርና አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችን የልማት ክፍተት በጥናት በመለየት የሚለሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ የግል ባለሀብቶችም በልማቱ እንዲሳተፉ ያበረታታል፤

a) promote the country's tourism resources and attractions domestically and abroad by organizing and coordinating tourism marketing initiatives of the various stakeholders;

b) establish and administer tourism fund to carry out its mandates;

c) design and implement a strategy to ensure that the country's tourist attractions are identified, properly developed and organized; set up, coordinate and direct gateways in country tourism attractions and facilities information centers;

d) improve conditions and work towards fulfillment of preconditions of the nation's tourist attractions for recognition as international heritages;

e) originate and put into effect tourism attraction, product and service brands and update them timely

f) identify, collect, analyze, organize and communicate data and study types suitable for conducting marketing operations;

g) set tourist service provider institution standards and supervise same;

h) ensure that tourist services are expanded and that local communities share the benefits derived from tourism;

i) facilitate the addressing of training needs by assessing tourism development and marketing service gap;

j) establish collaboration and partnership with various actors in the tourism sector;

k) conduct studies and research to ensure growth of the tourism sector; implement same when it is approved by the relevant organ;

l) identify existing and new tourist destinations development gaps and facilitate their development, and promote the participation of the private sector in the development of same;

ኘ) የሰመረ የቱሪዝም አገልግሎት እንዲኖር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፣ የመንግሥትና የግል ዘርፍ አካላትን ያስተባብራል፣ ከክልል የቱሪዝም አካላት ጋር በጋራ የሚሰራበትን ማዕቀፍ በማዘጋጀት በሥራ ላይ ያውላል፤ ጥራት ያለው የቱሪዝም አገልግሎትና የቱሪስቶችን ደህንነት ለማረጋገጥ ያሉትን ዘርፈ-ብዙ ጥረቶች ለማስተባበር በቱሪዝም ዙሪያ ለሚፈጠሩ የጋራ መድረኮች በማዕከልነት ያገለግላል፤

ነ) በውጭ አገር ከሚገኙ አቻ ተቋማት ጋር ትብብራዊ ግንኙነት ይመሰርታል።

፫. የአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

ሀ) በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉት የአካባቢ ደህንነት ዓላማዎችና በአገሪቱ የአካባቢ ፖሊሲ የተመለከቱት መሠረታዊ መርሆዎች ከግብ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራትን ያስተባብራል;

ለ) በመንግሥትም ሆነ በግል የሚወጡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ ሥልቶች፣ ሕጎች መርሐ ግብሮች እና ፕሮጀክቶች ላይ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ወይም ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ሥርዓቱ በተግባር ላይ መዋሉንም ይከታተላል፤

ሐ) ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ፍትህን በሚያራምድና ከሚገኘው ጥቅም ትልቁን ድርሻ በእርምጃው ለሚነኩ ማህበረሰቦች በሚያስገኝ አካሄድ ከደን ምንጣሮና ጉስቁልና ሊከተል ይችል የነበረውን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት የመቀነሻ ሥርዓት ያዘጋጃል፤

መ) ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን በየዘርፉና በየክልሉ ለመገንቢያ የሚውል ሃብት የሚያስገኙ ተግባራት ዝግጅትን ያስተባብራል፤ የአቅም ግንባታ ድጋፍንና የምክር አገልግሎትን ይሰጣል፤

ሠ) በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ መሠረት ለልማት ፕሮጀክት እና ፕሮግራም የይሁንታ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት የፕሮጀክቱ እና ፕሮግራሙ ትግበራ በአካባቢ ላይ የሚያስከትለው

m) work in cooperation with relevant actors to ensure coordinated tourism services; coordinate the actions of government and private entities; formulate and implement frameworks to forge cooperation among regional tourism organs; serve as a focal point for forums established to facilitate the coordination of multi-sectoral efforts required for the provision of quality tourist services and for ensuring the wellbeing of tourists;

n) establish alliance with overseas similar institutions.

3. The Environment, Forest and Climate Change Commission is hereby established. The Commission shall have the powers and duties to:

a) coordinate activities to ensure that the environmental objectives provided under the Constitution and the basic principles set out in the Environmental Policy of the Country are realized;

b) establish a system that enables undertaking environmental impact assessment or strategic environmental assessment of social and economic development polices, strategies, laws, program and projects set by the government or private entities, and fololow up the implementation of same;

c) prepare a mechanism that promotes social, economic and environmental justice and channel the major part of the benefit derived thereof to the affected communities to reduce emissions of greenhouse gases that would otherwise have resulted from deforestation and forest degradation;

d) coordinate actions on soliciting the resources required for building a climate resilient green economy in all sectors and at all Regional levels; provide capacity building support and advisory services on same;

e) establish a system for evaluating and deciding on the impacts of implementing investment programs and projects on the environment, in accordance with the

አሉታዊ ተፅዕኖ በሚመለከተው የዘርፍ የፈቃድ ሰጪ አካል ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ተገምግሞ ውሣኔ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ትግበራውንም ያረጋግጣል፤

ረ) ኢትዮጵያ ከተፈጥሮ ሃብቶች መሠረት፣ ከበረሀማነት፣ ከደን፣ ከአደገኛ ኬሚካሎች፣ ከኢንዱስትሪ ቆሻሻዎች እና ከሰው ሰራሽ የአካባቢ አደገኛ ንጥረ ነገሮች ጋር በተያያዘ ያፀደቀቻቸው አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የአካባቢ ስምምነቶችን በየዘርፉና በየአስተዳደር እርከኑ በመተግበር ወቅት የድግግሞሽ፣ የሃብት ብክነትንና ክፍተትን ለማስቀረት የሚያስችሉ መርሐግብሮችን እና መመሪያዎችን ያዘጋጃል፤ መተግበራቸውንም ይከታተላል፤

ሰ) በዓለም አቀፍ የአካባቢ እና የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነቶች ድርድር ላይ ይሳተፋል፣ በዘርፉ አገራዊ ምላሽን በማስተባበሩ በኩል ቁልፍ ሚና ይጫወታል፣ እንደአግባቡ ስምምነቶቹ እንዲፀድቁ ሃሳብ ያቀርባል፤

ሸ) ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸውን፣ ዓለም አቀፍ የአካባቢ ውሎች ለመተግበር ተፈላጊ የሆኑ ፖሊሲዎችን፣ ስልቶችን፣ ሕጎችንና መርሐ ግብሮችን እንደሁኔታው ያዘጋጃል፣ ወይም እንዲዘጋጁ ሃሳብ ያመነጫል፣ አዘገጃጀታቸውን ያስተባብራል፤ ሲፈቀዱም በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

ቀ) አደገኛ ንጥረ ነገሮችን ወይም ዝቃጮችን ማምረትን፣ ወደ ሀገር ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን፣ እንዲሁም ሕያዋንን በዘረመል ምሕንድስና መለወጥን፣ ለውጥ ወይም ባዕድ ሕያዋንን ወደ አገር ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን የሚመለከቱ የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲዎችንና ሕጎችን ያዘጋጃል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

በ) በልማት ዕቅዶችና በኢንቨስትመንት መርሐ ግብሮች ውስጥ የሚካተቱ የአካባቢ የአዋጪነት ማስሊያ ቀመሮችንና የስሌት ሥርዓቶችን ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ በጥቅም ላይ የመዋላቸውን ሂደት ይከታተላል፤

ተ) ዘላቂነት የጎደለው የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም ልምድን፣ የአካባቢ ጉስቁልናን ወይም ብክለትን ለመከላከል በሚያስችሉ የመግቻ እርምጃዎች ወይም የማበረታቻ ዘዴዎች መጠቀምን በተመለከተ ሃሣብ ያቀርባል፤

Environmental Impact Assessment Proclamation, prior to approvals of their implementation by the concerned sectoral licensing organ or the concerned Regional organ;

f) prepare programs and directives for the synergistic implementation and follow up of environmental agreements ratified by Ethiopia pertaining to the natural resources base, desertification, forests, hazardous chemicals, industrial wastes and anthropogenic environmental hazards with the objective of avoiding overlaps, wastage of resources and gaps during their implementation in all sectors and at all governance levels; follow up implementation of same;

g) take part in the negotiations of international environmental and climate change agreements and, as appropriate, initiate the process for their ratification; play a key role in coordinating the nationwide responses to the agreements;

h) formulate or initiate and coordinate the formulation of policies, strategies, laws, guidelines and programs to implement international environmental agreements to which Ethiopia is a party; and upon approval, ensure their implementation;

i) formulate environmental safety policies and laws on the production, importation, management and utilization of hazardous substances or wastes, as well as on the development of genetically modified organisms and the importation, handling and utilization of genetically modified organisms or alien species, and ensure their implementation;

j) prepare or cause the preparation of environmental cost benefit analysis and formulate an accounting system to be integrated in development plans and investment programs, as the case may be, monitor their application;

k) propose disincentives to discourage practices that may hamper the sustainable use of natural resources or incentives to encourage prevention of environmental degradation or pollution;

ቸ) የአካባቢ መረጃ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ሥርዓትን ይዘረጋል፤

ኀ) የአካባቢና የደን አያያዝን፣ በጥቅም ማዋልንና ፍትሃዊ የጥቅም ተጋሪነትን የሚያራምድ እንዲሁም አረንጓዴ የሥራ ዕድልን የሚፈጥር ምርምርንና የቴክኖሎጂ ሽግግርንያስተባብራል ፣እንደአስፈላጊነቱ ራሱ ያካሂዳል፤

ነ) አግባብነት ባላቸው የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የአካባቢና የደን ጥበቃ ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ በፌደራሉ ሥልጣን ሥር ወደሚገኝ ማንኛውም መሬት፣ ቅጥር ግቢ ወይም ሌላ ቦታ በመግባት ኃላፊነቱን ለመወጣት ተገቢ ሆኖ ያገኘውን ማንኛውንም ነገር ይፈትሻል፣ ናሙናዎችን ይወስዳል፤

ኘ) የአገሪቱን የአካባቢና የደን እንዲሁም ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን በሚመለከት ዘገባን በየወቅቱ እያዘጋጀ ያሰራጫል፤

አ) መደበኛ ያልሆኑ የአካባቢ ትምህርት መርሃ ግብሮችን ያስፋፋል፣ ትምህርቱን ይሰጣል፤ አካባቢያዊ ጉዳዮችን በመደበኛ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ለማካተት አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር ትብብር ያደርጋል፤

ከ) አነስተኛና ሰፋፊ የደን ልማት፣ ቀርከሀን ጨምሮ በግል፣ በወል ይዞታ እና በተፋሰስ ውስጥ እንዲለማና ጥቅም ላይ እንዲዉል ሥርዓት ይዘረጋል፣ትግበራውንም ያረጋግጣል፤

ኸ) የሀገሪቱ የተፈጥሮ ደን እንዲጠበቅና እንደአስፈላጊነቱ ዘላቂ ጥቅም ላይ እንዲዉል ሥርዓት ይዘረጋል፣ትግበራውንም ያረጋግጣል፤

ወ) የተጎዱና የተራቆቱ የደን መሬቶች እንዲያገግሙና የአካባቢያዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸው እንዲሻሻል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ትግበራውንም ያረጋግጣል።

፬. የስፖርት ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

ሀ) ሕዝቡን በስፖርት ለሁሉምና ባህላዊ ስፖርት ተሳታፊና ተጠቃሚ ያደርጋል፤

l) establish an environmental information system that promotes efficiency in environmental data collection, management and use;

m) coordinate, and as may be appropriate, carry out research and technology transfer activities that promotes the sustainability of the environment and the conservation and use of forest as well as the equitable sharing of benefits accruing from them while creating opportunities for green jobs;

n) in accordance with the provisions of the relevant laws, enter any land, premises or any other place that falls under the Federal jurisdiction, inspect anything and take samples as deemed necessary with a view to discharging its duty and ascertaining compliance with the requirements of environmental protection and conservation of forest;

o) prepare and disseminate a periodic report on the state of the country's environment and forest as well as climate resilient green economy;

p) promote and provide non-formal environmental education programs, and cooperate with the competent organs with a view to integrating environmental concerns in the regular educational curricula;

q) establish a system for development and utilization of small and large-scale forest including bamboo on private, communal and watershed areas, and ensure implementation of same;

r) establish a system for protection and, as the case may be, for sustainable utilization of the natural forest resources of the country; and ensure its implementation;

s) establish a system to rehabilitate degraded forest lands and ensure its implementation to enhance their environmental and economic benefits.

4. The Sport Commission is hereby established. The Commission shall have the powers and duties to:

a) enable the public to participate in and benefit from sports-for-all and traditional sports;

ለ) የሰለጠነ የሰው ሃይል ማፍራትና ብቃትን ለማሳደግ የስፖርት ትምህርት፣ ሥልጠናና ምርምር ተቋሞች የሚቋቋሙበትን ሥልት በመቀየስ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

ሐ) የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችንና የስፖርት ማበልጸጊያ ማዕከላትን ያስፋፋል፤

መ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ሕክምና አገልግሎት ያደራጃል፤ በስፖርት አበረታች መድኃኒቶችና ዕፆች መጠቀምን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

ሠ) የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል፤ በፌደራል ደረጃ የሚቋቋሙ የስፖርት ማህበራትን ይመዘግባል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።

፭. የተፋሰሶች ልማት ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን በተፋሰሶች ውስጥ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚረዱ የፖሊሲ ጥናቶችን፣ ቅኝቶችና ምርምሮችን ያደርጋል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ይተገብራል፤

ለ) በተፋሰሶች ውስጥ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደትን ለማስፈጸም የሚረዱ ተግባራትን ያከናውናል፣ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

ሐ) በተፋሰሶች ውስጥ የሚተገበሩ ከውሃ ጋር የተገናኙ ፕሮጀክቶችና እንቅስቃሴዎች በይዘታቸው፣ በጊዜ ሠሌዳቸው፣ በውጤታቸውና በአመራራቸው ከተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

መ) የተፋሰሶችን ጥበቃና ዘላቂ ጥቅም በተመለከተ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

ሠ) የተፋሰሶችን ውሃ ሀብት ስትራቴጂክ ዕቅድና የውሃ አስተዳደር ተግባራትን ለመምራትና ለመደገፍ እንዲያስችል የተፋሰስ ሞዴል ያዘጋጃል፣ ይጠቀማል፤

ረ) ተፋሰሶችን ከብክለትና ከጉዳት ለማዳን ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች በጥናት ይለያል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይተገብራል፤

b) design and implement strategies for the establishment of sport education, training and research institutions to produce trained manpower and to improve competence;

c) promote the expansion of sports facilities and centers;

d) organize sports medical facilities in cooperation with the appropriate bodies, and adopt systems for controlling doping practices;

e) issue directives governing the establishment of sports associations; register and support associations operating at the federal level.

5. The Basins' Development Authority is hereby established. The Authority shall have the powers and duties to:

a) undertake policy studies, surveys and researches needed to create a conducive environment for the implementation of an integrated water resource management within basins; and follow up implementation upon approval by the relevant body;

b) facilitate and undertake activities necessary for the implementation of integrated water resources management in basins;

c) ensure that projects, activities and interventions related to water in basins, in their content, schedule, impacts and management, are in line with integrated water resource management process;

d) develop plans for protection and sustainable use of basins; follow up implementation once it is approved by the relevant organ;

e) develop and implement basin models in order to guide and support strategic planning of water resources and water administration functions;

f) identify measures that should be taken against pollution and damage to basins; implement same in collaboration with relevant organs;

ሰ) ለክልሎች በሕግ የተሰጠ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በተፋሰሶች ውስጥ በውሃ ለመጠቀምና ውሃ ነክ ሥራዎች ለመሥራት የሚያስችል ፈቃድ ይሰጣል፣ በፈቃዱ ላይ ሁኔታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

ሸ) በተፋሰሶች ውስጥ የሚደረጉ የመስኖ ማስፋፋት ሥራዎችን ለመደገፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፤

ቀ) የወንዝ አቅጣጫ አመራር ሥራ ይሠራል፤

በ) ከተጠቃሚዎች የውሃ ክፍያ ይሰበስባል፤

ተ) በተፋሰሶች የሚገኘውን የውሃ ሀብት በተገቢው ሁኔታ ለማቀድ፣ ለማስተዳደርና ለማንቀሳቀስ የሚጠቅሙ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል ፣ይተነትናል፣ ያሠራጫል፤

ቸ) የውሃ ምደባንና አጠቃቀምን በተመለከተ የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት ለውሃ፣ መስኖና ኤነርጂ ሚኒስቴር ተገቢውን የምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ይሠጣል፤

ኀ) ከክልል መንግሥት አካላት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ውጤታማ የግንኙነት መድረክ በመፍጠር ቀጣይነት ያለው ትብብር እንዲፈጠር ያደርጋል፤

ነ) ድንበር ዘለል ወንዞችን በሚመለከት ከሌሎች አገሮች ጋር ለመወያየት አግባብ ላለው አካል አስፈላጊ መረጃዎችን አዘጋጅቶ ይሠጣል።

፮. የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን በሥራ ላይ ባሉ ሕጎችና ድንጋጌዎች ከተሠጡት ሥልጣንና ተግባራት በተጨማሪ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፷፯/፲፱፻፺፪ ዓ.ም ለመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት ሁሉ በዚህ አዋጅ ለብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ተሰጥተዋል።

፯. በሥራ ላይ ባሉ ሕጎችና ድንጋጌዎች የግብርና ኢንቨስትመንትን በተመለከተ ለሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለግብርና ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፤ የሆርቲካልቸር ዘርፉን ልማት በተመለከተ ለባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ተሰጥተዋል።

g) without prejudice to the powers given to Regional States, issue permits applicable to basins' water use and water works, and ensure that the terms of the permits are complied with;

h) work in collaboration with relevant organs to support efforts to expand irrigation works within basins;

i) undertake administration of river training activity;

j) collect water charges from users;

k) collect, compile, analyze and disseminate information for proper planning, administration and steering of water resources in basins;

l) give advice and technical support to the Ministry of Water, Irrigation and Energy on dispute resolution in relation to the allocation and use of water resources in basins;

m) ensure continuous collaboration with Regional Government organs and other relevant bodies by setting up a forum for effective networking;

n) prepare and provide the necessary information on trans-boundary basins to the concerned body in charge of negotiations with other countries.

6. In addition to the powers and duties given to National Disaster Risk Management Commission under existing laws, the powers and duties given to the Emergency Food Security Reserve Administration under Council of Ministers Regulations Number 67/2000 are hereby vested in the Commission.

7. The powers and duties given to the Horticulture and Agriculture Investment Authority by the provision of other laws currently in force pertaining to agricultural investment are hereby vested in the Ministry of Agriculture; those powers and duties pertaining to development of horticulture sector are hereby vested in the Ethiopian Investment Commission.

፰. የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል። በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፵፯/፪ሺ፬ ዓ.ም ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንፎርሜሽን ማዕከል ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት ሁሉ በዚህ አዋጅ ለቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲቲዩት ተሰጥተዋል።

፱. የጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲቲዩት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል። በኢትዮጵያ ጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፱/፪ሺ፲ ዓ.ም ለጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኤጀንሲ፣ እንዲሁም ጂኦስፓሻል ዳታና መረጃን በተመለከተ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፰//፪ሺ፮ ዓ.ም ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት ለጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲቲዩት ተሰጥተዋል።

፲. የገቢዎች ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል። በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፹፯/፪ሺ ዓ.ም ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለገቢዎች ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

፲፩. የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲቲዩት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል። በኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲቲዩት ማቋቋሚያ የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፶፬/፲፱፻፺፩ ዓ.ም ለኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲቲዩት፣ እና በሥራ ላይ ባሉ ሕጎችና ድንጋጌዎች ለፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ሁሉ በዚህ አዋጅ ለፖሊሲ ጥናት ኢንስቲቲዩት ተሰጥተዋል።

፲፪. የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት የሚወስን ደንብ ያወጣል።

፲፫. የሥራ ዕድል ፈጠራ ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባራት የሚወስን ደንብ ያወጣል።

፲፬. የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት የሚወስን ደንብ ያወጣል።

8. The Technology and Innovation Institute is hereby established. The powers and duties given to the Science and Technology Information Center under Council of Ministers Regulations Number 247/2011 is hereby vested in the Institute.

9. The Geospatial Information Institute is hereby established. The powers and duties given to the Geospatial Information Agency under its establishment Proclamation Number 1079/2018 and powers and duties given to the Information Network Security Agency under Proclamation Number 808/2013 are hereby vested in the Institute.

10. The Ministry of Revenues is hereby established. The powers and duties given to the Ethiopian Revenues and Customs Authority under the Ethiopian Revenues and Customs Authority Establishment Proclamation Number 587/2008 are hereby vested in the Ministry.

11. The Policy Research Institute is hereby established. The powers and duties given to the Ethiopian Development Reasearch Institute under the Ethiopian Development Research Institute Council of Ministers Establishment Regulations 54/1999 and the powers and duties given to the Policy Study and Research Center under existing laws are hereby vested in the Policy Research Institute.

12. The Immigration, Nationality and Vital Events Agency is hereby established. The Council of Ministers shall issue Regulations determining the powers and duties of the Agency.

13. The Job Creation Commission is hereby established. The Council of Ministers shall issue Regulations determining the powers and duties of the Commission.

14. The Refugees and Returnees Affairs Agency is hereby established. The Council of Ministers shall issue Regulations determining the powers and duties of the Agency.

፲፭. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት የሚወስን ደንብ ያወጣል።

፲፮.የኮንስትራክሽን ሥራዎች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት የሚወስን ደንብ ያወጣል።

፲፯. የመስኖ ልማት ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባራት የሚወስን ደንብ ያወጣል።

፲፰. የውሃ ልማት ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባራት የሚወስን ደንብ ያወጣል።

፲፱. የፕላንና ልማት ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል። በብሔራዊ ፕላን ምክር ቤትና የብሔራዊ ፕላን ኮሚሽን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፪፻፹፩/፪ሺ፭ ዓ.ም ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለገቢዎች ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## ፴፫. ተጠሪ የፌደራል አስፈጻሚ አካላት

፩. በሚከተሉት ንዑስ አንቀጾች የተደረጉት የተጠሪነት ማሻሻያዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የፌደራል መንግሥቱ ሌሎች አስፈጻሚ አካላት በተቋቋሙባቸው ሕጎች በተደነገገው መሠረት ሥራቸውን ይቀጥላሉ።

፪. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሆናል:-

ሀ) የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን
ለ) የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን
ሐ) የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
መ) የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት
ሠ) የፌደራል ሥነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን

፫. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል:-

ሀ) የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን
ለ) የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

15. The Public Enterprises Holding and Adminstration Agency is hereby established. The Council of Ministers shall issue Regulations determining the powers and duties of the Agency.

16. The Construction Works Regulatory Authority is hereby established. The Council of Ministers shall issue Regulations determining the powers and duties of the Authority.

17. The Irrigation Development Commission is hereby established. The Council of Ministers shall issue Regulations determining the powers and duties of the Commission.

18. The Water Development Commission is hereby established. The Council of Ministers shall issue Regulations determining the powers and duties of the Commission.

19. The Planning and Development Commission is hereby established. The powers and duties given to the National Planning Commission under the National Planning Council and National Planning Commission Council of Ministers Establishment Regulations Number 281/2013 are hereby vested in the Planning and Development Commission.

## 33. Accountable Federal Executive Organs

1. Without prejudice to the amendments made under the provisions of the following sub-articles with regard to accountability, other Federal executive organs shall continue their function in accordance with the legislations establishing them.
2. The following Executive Organs shall be accountable to the House of People's Representatives:
   a) the Ethiopian Broadcasting Authority
   b) the Ethiopian Broadcasting Corporation
   c) the Ethiopian Press Agency
   d) the Ethiopian News Agency
   e) the Federal Ethics and Anti-Corruption Commission
3. The following executive organs shall be accountable to the Prime Minister:
   a) the Ethiopian Investment Commission
   b) the Civil Service Commission

ሐ) የአካባቢ፣ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን

መ) የሥራ ዕድል ፈጠራ ኮሚሽን

ሠ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

ረ) ቱሪዝም ኢትዮጵያ

ሰ) የቤተ-መንግሥት አስተዳደር

፬. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለሰላም ሚኒስቴር ይሆናል:-

ሀ) የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት

ለ) የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ

ሐ) የፋይናንስ ደኅንነት መረጃ ማዕከል

መ) የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን

ሠ) የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ

ረ) የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ

ሰ) የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን

ሸ) የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ስትራቴጂክ ጥናት ኢንስቲቲዩት

፭. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለአገር መከላከያ ሚኒስቴር ይሆናል:-

ሀ) የአገር መከላከያ ኢንጂነሪንግ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ

ለ) ጋፋት አርማሜንት

ሐ) ሆሚቾ አሙኒሽን ኢንጂነሪንግ

መ) ደጀን አቪየሽን ኢንጂነሪንግ

ሠ) ብራና ማተሚያ ድርጅት

ረ) የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ

ሰ) የመከላከያ ኮንስትራክሽን ዲዛይን ድርጅት

ሸ) የመከላከያ ኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት

፮. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይሆናል:-

ሀ) የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት

ለ) የዲያስፖራ ኤጀንሲ

፯. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለገንዘብ ሚኒስቴር ይሆናል:-

ሀ) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ

c) the Environment, Forest and Climate Change Commission

d) the Job Creation Commission

e) the Ethiopian National Bank

f) the Tourism Ethiopia

g) the Palace Administration

4. The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Peace:

a) the National Information Security Service

b) the Information Network Security Agency

c) the Finance Security Information Center

d) the Federal Police Commission

e) the Immigration, Nationality and Vital Events Agency

f) the Immigrants and Returnees Affairs Agency

g) the National Disaster Risk Management Commission

h) the Ethiopian Foreign Relations Strategic Studies Institute

5. The following executive organs shall be accountable to the Ministry of National Defense:

a) National Defense Engineering University College

b) Gafat Armament

c) Homicho Ammunition Engineering

d) Dejena Aviation Engineering

e) Brana Printing Press

f) Defense Construction Enterprise

g) Defense Construction Design Enterprise

h) Defense Construction Materials Production Factory

6. The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Foreign Affairs:

a) the Foreign Relations Services Training Institute

b) the Diaspora Agency

7. The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Finance:

a) the Public Enterprises Holding and Administration Agency

ለ) የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ

ሐ) የመንግሥት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ

መ) የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት

፰. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ይሆናል:-

ሀ) የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ

ለ) የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት

ሐ) የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር

መ) የፍትህና የሕግ ምርምርና ሥልጠና ኢንስቲቲዩት

ሠ) የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ

ረ) የፌደራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ

፱. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለግብርና ሚኒስቴር ይሆናል:-

ሀ) የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት

ለ) የግብርና ምርምር ካውንስል ሴክሬታሪያት

ሐ) የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ

መ) የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ

ሠ) የቡናና ሻይ ልማትና ግብይት ባለሥልጣን

ረ) የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች

ሰ) የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን

ሸ) ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርምርና ጥናት ማዕከል

ቀ) የብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል

በ) የብሔራዊ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት

ተ) ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት

፲. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ይሆናል:-

ሀ) የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

ለ) የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

b) the Ethiopian Accounting and Auditing Board

c) the Public Procurement and Property Administration Agency

d) the Public Procurement and Property Disposal Service

8. The following executive organs shall be accountable to the Attorney General:

a) the Charities and Societies Agency

b) the Ethiopian Intellectual Property Office

c) the Federal Prisons Administration

d) the Justice and Legal Research and Training Institute

e) the Documents Authentication and Registration Agency

f) the Federal Tax Appeal Tribunal

9. The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Agriculture:

a) the Ethiopian Institute of Agricultural Research

b) the Agricultural Research Council Secretariat

c) the Cooperatives Agency

d) the Agricultural Transformation Agency

e) the Coffee and Tea Development and Marketing Authority

f) the Agriculture Technical and Vocational Education and Training Colleges

g) the Veternary Drug and Animal Feed Administraiton and Control Authority

h) the National Animal Health Diagnostic and Investigation Center

i) the National Artificial Insemination Center

j) the National Institute for Control and Eradidcation of Tsetse Fly and Trypanosomosis;

k) the National Veternary Institute

10. The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Trade and Industry:

a) the Textile Industry Development Institute

b) the Leather Industry Development Institute

ሐ) የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

መ) የምግብ፣ የመጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

ሠ) የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

ረ) የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

ሰ) የፌደራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ማስፋፊያ ባለሥልጣን

ሸ) የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን

ቀ) የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን

በ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽ/ቤት

ተ) የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ

ቸ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት

ኀ) የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ኤጀንሲ

ነ) የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅራቢ ልማት ድርጅት

፲፩. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ይሆናል:-

ሀ) የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከል ባለሥልጣን

ለ) የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

ሐ) የኢትዮጵያ ባዮቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት

መ) የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲቲዩት

ሠ) የጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲቲዩት

፲፪. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ይሆናል:-

ሀ) የኢትዮጵያ ሲቪል አቪየሽን ባለሥልጣን

ለ) የፌደራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን

ሐ) የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን

መ) የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን

ሠ) የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት

ረ) የመድህን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ

ሰ) የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን

c) the Metals Industry Development Institute

d) the Food, Beverage and Pharmaceutical Industry Development Institute

e) the Chemical and Construction Inputs Industry Development Institute

f) the Meat and Diary Industry Development Institute

g) the Federal Small and Medium Manufacturing Industry Development Authority

h) the Ethiopian Trade Competition and Consumers Protection Authority

i) the Ethiopian Commodity Exchange Authority

j) the Ethiopian National Accreditation Office

k) the Ethiopian Standards Agency

l) the National Metrology Institute of Ethiopia

m) the Ethiopian Conformity Assessment Enterprise

n) the Industrial Inputs Development Enterprise

11. The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Innovation and Technology:

a) the Ethiopian Radiation Protection Authority

b) the Ethiopian Space Science and Technology Institute

c) the Ethiopian Biotechnology Institute

d) the Technology and Innovation Institute

e) the Geospatial Information Institute

12. The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Transport:

a) the Ethiopian Civil Aviation Authority

b) the Federal Transport Authority

c) the Maritime Affairs Authority

d) the Ethiopian Roads Authority

e) the Road Fund Office

f) the Insurance Fund Adminstration Agency

g) the Ethiopian Railroad Corporation

ሸ) የኢትዮ-ጅቡቲ ስታንዳርድ ጌጅ ባቡር ትራንስፖርት አ.ማ.

ቀ) የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት

በ) የኢትዮጵያ ክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ

፲፫. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ይሆናል:-

ሀ) የፌደራል ከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ

ለ) የፌደራል ከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ

ሐ) የተቀናጀ መሠረተ-ልማት ማስተባበሪያ ኤጀንሲ

መ) የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት

ሠ) የኮንስትራክሽን ሥራዎች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

ረ) የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን

፲፬. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ይሆናል:-

ሀ) የመስኖ ልማት ኮሚሽን

ለ) የውሀ ልማት ኮሚሽን

ሐ) የተፋሰሶች ልማት ባለሥልጣን

መ) የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት

ሠ) የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

ረ) ብሔራዊ የሜትሪዮሎጂ ኤጀንሲ

ሰ) የኢትዮጵያ ኤነርጂ ባለሥልጣን

ሸ) የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

ቀ) የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት

፲፭. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ይሆናል:-

ሀ) የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ

ለ) የኢትዮጵያ የገጠር ኤነርጂ ልማት ማስፋፊያ ማዕከል

ሐ) የኢትዮጵያ ነዳጅና ጋዝ ምርትና አቅርቦት ኮርፖሬሽን

፲፮. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል:-

h) the Ethio-Djibouti Standard Gauge Railway Transport S.C.

i) the Public Service Transport Service Enterprise

j) the Ethiopian Toll Roads Enterprise

13. The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Urban Development and Construction:

a) the Federal Urban Real Property Registration and Information Agency

b) the Federal Urban Job Opportunities Creation and Food Security Agency

c) the Integrated Infrastructure Development Coordination Agency

d) the Construction Project Management Institute

e) the Construction Works Regulatory Authority

f) the Federal Houses Corporation

14. The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Water, Irrigation and Energy:

a) the Irrigation Development Commission

b) the Water Development Commission

c) the Basins Development Authority

d) the Great Renaissance Dam Coordination Project Office

e) the Water Technology Institute

f) the National Meteorology Agency

g) the Ethiopian Energy Authority

h) the Ethiopian Electric Power

i) the Ethiopian Electric Utility

15. The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Mines and Petroleum:

a) the Ethiopian Geological Survey

b) the Ethiopian Rural Energy Development and Promotion Center

c) the Ethiopian Petroleum and Gas Production and Supply Corporation

16. The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Education:

ሀ) የአገር አቀፍ ትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ

ለ) የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት

፲፯. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል:-

ሀ) የከፍተኛ ትምህርት ስትራቴጂክ ማዕከል

ለ) የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ

ሐ) የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ

መ) የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች

ሠ) የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ

ረ) የፌደራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ

ሰ) የፌደራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት

፲፰. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለጤና ሚኒስቴር ይሆናል:-

ሀ) ቅዱስ ጴጥሮስ ቲቢ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል

ለ) ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልና ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ

ሐ) ቅዱስ አማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል

መ) የመላ አፍሪካ ሥጋ ደዌ መከላከያና ትምህርት መስጫ ማዕከል

ሠ) የኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን

ረ) የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት

ሰ) የመድኃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ

ሸ) የኢትዮጵያ ጤና መድህን ኤጀንሲ

ቀ) ብሔራዊ የደም ባንክ አገልግሎት

በ) የአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት

ተ) ብሔራዊ የኤች. አይ. ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት

፲፱. የግል ድርጅት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ተጠሪነት ለሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ይሆናል።

፳. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ይሆናል፡-

a) the National Educational Assessment and Examination Agency

b) the Educational Materials Production and Distribution Enterprise

17. The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Science and Higher Education:

a) the Higher Education Strategic Center

b) the Addis Ababa Science and Technology University

c) the Adama Science and Technology University

d) Government Universities

e) the Higher Education Relevance and Quality Agency

f) the Federal Technical and Vocational Education and Training Agency

g) the Federal Technical and Vocational Education and Training Institute

18. The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Health:

a) the St. Peter’s TB Specialized Hospital

b) the St. Paul’s Hospital and Millenium Medical College

c) the St. Amanuel Mental Specialized Hospital

d) the All Africa Leprosy and Rehabilitation Training Center

e) the Ethiopian Food, Medicine, and Health Care Administration and Control Authority

f) the Ethiopian Public Health Institute

g) the Pharmaceutical Supply Agency

h) the Ethiopian Health Insurance Agency

i) the National Blood Bank Services Office

j) the Armauer Hansen Research Institute

k) the Federal HIV/AIDS Prevention and Control Office

19. The Private Organizations’ Employees Social Security Agency shall be accountable to the Ministry of Labor and Social Affairs.

20. The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Culture and Tourism:

ሀ) የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን

ለ) ብሔራዊ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መፃህፍት ኤጀንሲ

ሐ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር

መ) የሆቴሎችና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል

ሠ) የስፖርት ኮሚሽን

፳፩. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለገቢዎች ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የጉምሩክ ኮሚሽን

ለ) የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር

፳፪. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለፕላንና ልማት ኮሚሽን ይሆናል፡-

ሀ) ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

ለ) የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት

፳፫. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ይሆናል:-

ሀ) የሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ

ለ) መለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ

ሐ) የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት

መ) የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት

ሠ) የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

፳፬. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ይሆናል:-

ሀ) የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን

ለ) የመሬት ባንክና ልማት ኮርፖሬሽን

፳፭. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለአካባቢ ጥበቃ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ይሆናል፡-

ሀ) የኢትዮጵያ ብዝሃ-ሕይወት ኢንስቲትዩት

ለ) የኢትዮጵያ አካባቢና ደን ምርምር ኢንስቲትዩት

ሐ) የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን

፳፮. የውሃ ልማት ፈንድ ተጠሪነት ለውሃ ልማት ኮሚሽን ይሆናል።

a) the Authority for Research and Conservation of Cultural Heritage

b) the National Archives and Library Agency

c) the National Theatry

d) the Hotels and Tourism Works Training Center

e) the Sport Commission

21. The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Revenues :

a) the Customs Commission

b) the National Lottery Administration

22. The following executive organs shall be accountable to the Planning and Development Commission:

a) the Central Statistics Agency

b) the Policy Research Institute

23. The following executive organs shall be accountable to the Civil Service Commission:

a) the Civil Service University

b) the Meles Zenawi Leadership Academy

c) the Ethiopian Kaizen Institute

d) the Ethiopian Management Institute

e) the Public Servants Social Security Agency

24. The following executive organs shall be accountable to the Ethiopian Investment Commission:

a) the Industrial Parks Development Corporation

b) the Land Bank and Development Corporation

25. The following executive organs shall be accountable to the Environment, Forest, and Climate Change Commission:

a) the Ethiopian Biodiversity Institute

b) the Ethiopian Environment and Forest Research Institute

c) the Ethiopian Wildlife Conservation Authority

26. The Water Development Fund shall be accountable to the Water Development Commission.

፳፯. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለስፖርት ኮሚሽን ይሆናል፡-

ሀ) የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ

ለ) አትሌት ጥሩነሽ ዲባባ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል

ሐ) ፀረ-አበረታች ቅመሞች ጽ/ቤት

**፴፬. <u>የፌደራል አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ስለማደራጀት</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ደንብ በማውጣት፣ማንኛውም አስፈጻሚ አካል እንዲታጠፍ፣ ከሌላ አስፈጻሚ አካል ጋር እንዲዋሃድ ወይም እንዲከፋፈል በማድረግ፣ ተጠሪነቱ ወይም ሥልጣንና ተግባሩ እንዲለወጥ በማድረግ ወይም አዲስ አስፈጻሚ አካል እንዲቋቋም በማድረግ የፌደራል አስፈጻሚ አካላትን እንደገና የማደራጀት ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

**<u>ክፍል አራት</u>**

**<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>**

**፴፭. <u>የተሻሩ ሕጎች</u>**

፩. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ (እንደተሻሻለ) በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

፪. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ሕግ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚ አይሆንም።

**፴፮. <u>መብትና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ</u>**

፩. የፌደራልና አርብቶ አደር አካባቢ ልማት ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለሰላም ሚኒስቴር ተላልፈዋል።

፪. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለገንዘብ ሚኒስቴር ተላልፈዋል።

፫. የብሔራዊ ፕላን ኮሚሽን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለፕላንና ልማት ኮሚሽን ተላልፈዋል።

፬. የግብርናና እንስሳት ሃብት ሚኒስቴር እንዲሁም የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለግብርና ሚኒስቴር ተላልፈዋል።

፭. የንግድ ሚኒስቴር እና የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተላልፈዋል።

27. The following executive organs shall be accountable to the Sport Commission:

a) the Ethiopian Youth Sport Academy

b) the Athlete Tirunesh Dibaba Athletics Training Center

c) the Anti-Doping Office

**34. <u>Reorganization of Federal Executive Organs</u>**

The Council of Ministers is hereby empowered, where it finds it necessary, to reorganize the Federal executive organs by issuing regulations for the closure, merger or division of an existing executive organ or for change of its accountability or mandates or for the establishment of a new one.

**<u>PART 4</u>**

**<u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>**

**35. <u>Repealed Laws</u>**

1. Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015 (as amended) is hereby repealed.
2. No laws or practices shall, in so far as they are inconsistent with this Proclamation, have force or effect with respect to matters provided for by this Proclamation.

**36. <u>Transfer of Rights and Obligations</u>**

1. The rights and obligations of Ministry of Federal Affairs and Pastoral Development are hereby transferred to Ministry of Peace.
2. The rights and obligations of Ministry of Finance and Economic Cooperation are hereby transferred to Ministry of Finance.
3. The rights and obligations of National Planning Commission are hereby transferred to Planning and Development Commission
4. The rights and obligations of Ministry of Agriculture and Livestock and Ethiopian Horticulture and Agricultural Investment Authority are hereby transferred to Ministry of Agriculture.
5. The rights and obligations of Ministry of Trade and Ministry of Industry are hereby transferred to Ministry of Trade and Industry.

፮. የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች እንዲሁም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተላልፈዋል።

፯. የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር እና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተላልፈዋል።

፰. የዉሃ ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለውሃ፣ መስኖና ኤነርጂ ሚኒስቴር ተላልፈዋል።

፱. የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተላልፈዋል።

፲. የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ተላልፈዋል።

፲፩. ከፍተኛ ትምህርትና የቴክኒክና ሙያ ሥልጠናን በተመለከተ የትምህርት ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ተላልፈዋል።

፲፪. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለጤና ሚኒስቴር ተላልፈዋል።

፲፫. በወጣቶችና ስፖርት ኮሚሽን ወጣቶችን የሚመለከቱ መብትና ግዴታዎች፣ እንዲሁም የሴቶችና የሕፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር ተላልፈዋል።

፲፬. በወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ስፖርትን የሚመለከቱ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለስፖርት ኮሚሽን ተላልፈዋል።

፲፭. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለገቢዎች ሚኒስቴር ተላልፈዋል።

፲፮. የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲቲዩት እና የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለፖሊሲ ጥናት ኢንስቲቲዩት ተላልፈዋል።

6. The rights and obligations of Ministry of Communications and Information Technology and the Ministry of Science and Technology are hereby transferred to Ministry of Innovation and Technology.

7. The rights and obligations of Ministry of Urban Development and Housing and Ministry of Construction are hereby transferred to Ministry of Urban Development and Construction.

8. The rights and obligations of Ministry of Water, Irrigation and Electric are hereby transferred to Ministry of Water, Irrigation and Energy.

9. The rights and obligations of the Ministry of Public Service and Human Resources are hereby transferred to the Civil Service Commission.

10. The rights and obligations of Ministry of Mines, Petroleum and Natural Gas are hereby transferred to Ministry of Mines and Petroleum.

11. The rights and obligations of Ministry of Education pertaining to higher education, and technical and vocational education are hereby transferred to Ministry of Science and Higher Education.

12. The rights and obligations of Ministry of Health are hereby transferred to Ministry of Health.

13. The rights and obligations of Ministry of Women and Children Affairs and Ministry of Youth and Sport relating to youth are hereby transferred to Ministry of Women, Children and Youth.

14. The rights and obligations of Ministry of Youth and Sport relating to sport are hereby transferred to Sport Commission

15. The rights and obligations of Ethiopian Revenue and Customs Authority are hereby transferred to Ministry of Revenue.

16. The rights and obligations of Ethiopian Development Research Institute and Policy Study and Research Center are hereby transferred to Policy Research Institute.

፲፯. የአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ተላልፈዋል።

፲፰. የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለቱሪዝም ኢትዮጵያ ተላልፈዋል።

፲፱. የኢንዱስትሪ ፕሮጀክት አገልግሎቶች መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ተላልፈዋል።

፳. የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ኤጀንሲ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ ተላልፈዋል።

፳፩. የስትራቴጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ተላልፈዋል።

፳፪. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ እና የመንግሥት ፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለገንዘብ ሚኒስቴር ተላልፈዋል።

፳፫. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ተላልፈዋል።

፳፬. የጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲቲዩት ተላልፈዋል።

፳፭. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንፎርሜሽን ማዕከል መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲቲዩት ተላልፈዋል።

፳፮. የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን፣ የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን እና የስምጥ ሸለቆ ተፋሰስ ባለሥልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተፋሰሶች ልማት ባለሥልጣን ተላልፈዋል።

፳፯. የኢትዮጵያ ባህል ማዕከል መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተላልፈዋል።

፳፰. የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተላልፈዋል።

17. The rights and obligations of Ministry of Environment, Forest and Climate Change are hereby transferred to Environment, Forest and Climate Change Commission.

18. The rights and obligations of the Ethiopian Tourism Organization are hereby transferred to Tourism Ethiopia.

19. The rights and obligations of the Industrial Project Services are hereby transferred to Industrial Parks Development Corporation.

20. The rights and obligations of Vital Events Registration Agency are hereby transferred to Immigration, Nationality and Vital Events Agency.

21. The rights and obligations of Strategic Food Reserve Agency are hereby transferred to National Disaster Risk Management Commission.

22. The rights and obligations of Public Enterprises Board of Trustees and Public Financial Enterprises Agency are hereby transferred to Ministry of Finance.

23. The rights and obligations of Ministry of Public Enterprises are hereby transferred to Public Enterprises Holding and Administration Agency.

24. The rights and obligations of Geospatial Information Agency are hereby transferred to Geospatial Information Institute.

25. The rights and obligations of Science and Technology Information Center are hereby transferred to the Technology and Innovation Institute.

26. The rights and obligations of Abay Basin Authority, Awash Basin Authority and Rift Valley Lakes Basin Authority transferred to the Basins Development Authority.

27. The rights and obligations pertaining to Ethiopian Cultural Center are hereby transferred to Ministry of Culture and Tourism.

28. The rights and obligations of Government Communications Affairs Office are hereby transferred to Civil Service Commission.

**፴፯. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፮ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሕዳር ፳ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**37. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on this 16th day of October, 2018

**Done at Addis Ababa, This 29th Day of November, 2018**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENTOFTHEFEDERALDEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**